# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን

## መመሪያ ቁጥር 537/2013 /እንደ ተሻሻለው/

ማውጫ

ክፍል

ጠቅላላ -------------------------------------------------------------------------------------------------------------- 1

ክፍል ሁለት

የምርት ገበያው ሥራ መጀመር ------------------------------------------------------------------------ 3

ክፍል ሦስት

ስለክፍያ መፈፀሚያ ተቋማት ተግባራትና ዕውቅና ---------- 14

ክፍል አራት

የማዕከላዊ ማከማቻ ሥራዎችን ስለመጀመር ---------- 23

ክፍል አምስት

የምርት ገበያው የግልግል ዳኝነት ---------- 26

ክፍል ስድስት

የምርት ግብይት ፈፃሚዎችን ዕውቅና ስለመስጠት ---------- 28

ክፍል ሰባት

ስለግብይት ፈፃሚዎች ንግድ አሰራር ---------- 36

ክፍል ስምንት

ስለብሄራዊ የግብይት ፈፃሚዎች ማህበር ዕውቅና ---------- 41

ክፍል ዘጠኝ

በባለሥልጣኑ ስለሚደረጉ ምርመራዎች ---------- 45

ክፍል አስር

በባለስልጣኑ አስተዳደራዊ ችሎት የጉዳዮች አወሳሰን ሥነ-ሥርዓቶች ---------- 52

ክፍል አስራ አንድ

ስለ ሕግ ጥሰቶችና ቅጣቶቻቸው ---------- 61

ክፍል አስራ ሁለት

የባለስልጣኑ የአስቸኳይ ጊዜ ስልጣኖች ---------- 64

ክፍል አስራ ሦስት

ማስታወቂያዎችን ስለማሳተም ---------- 66

ክፍል አስራ አራት

የክፍያዎች ሰንጠረዥ ---------- 66

ክፍል አስራ አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ---------- 67

<u>**የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን መመሪያ**</u>

የምርት ግብይት ስርዓቱን ለመቆጣጠር የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን በሕግ የተቋቋመ ስለሆነ፤

ባለስልጣኑ ወጤታማ የሆነ ዘመናዊ የማበያያ ስርዓት ማንባቱን የሚረጋገጥ፣ የምርት ገበያው አስተማማኝ፣ ግልጽና የተረጋጋ አሰራር እንዲኖረው የመቆጣጠር፣ እንዲሁም በገበያው የሚሳተፉትንም ሆነ በአጠቃላይ የህብረተሰቡን ጥቅም የማስጠበቅ ኃላፊነት ያለበት ስለሆነ፤

ይህንንም ለማድረግ ይቻል ዘንድ ዝርዝር መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በማኘቱ፤

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ 34/2/ መሠረት የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን መመሪያ ቁጥር 537/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡
2. **ዓላማ**

   የዚህ መመሪያ ዓላማ በምርት ገበያው ስለሚፈፀሙ ግብይቶች ማስረታዊያን፣ ስለ ምርት ግብይት ውሎች መርሆዎችና ስለገበያ አባልነት ቅድመ ሁኔታዎችን መወሰን፣ እንዲሁም የምርት ግብይት ውሎች ሽያጭና ግዥ በአስተማማኝ ደህንነትና በተረጋጋ ሁኔታ በነፃ ወድድር መርህ የሚፈጸሙ መሆናቸውን ሚረጋገጥ ነው፡፡
3. **ትርጉም**

   3.1. "የባለሥልጣኑ አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር 551/1999 እንደተሻሻለ ነው፡፡

   3.2. "ሥልጣን የተሰጠው ተወካይ" ማለት አባልን ስለንግድ ሥራው የሚወክል ሆኖ እንደ ግብይት ፈፃሚ ባለሥልጣኑ እውቅና ያገኘ ሰው ነው፡፡

   3.3. "ተባባሪ አባል" ማለት በአገናኝ አባል ሥር ሆኖ ለደንበኛው ጥቅም የሚገበያ አባል ነው፡፡

   3.4. "ቦርድ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 550/1999 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡

   3.5. "ማዕከላዊ ማከማቻ" ማለት በመጋዘን እቃ ላስቀመጡ ሰዎች ኤሌክትሮኒክ መጋዘን ደረሰኞችን በአደራ የሚያዝና በምርት ገበያው ላይ ግብይት ሲፈጸም ደረሰኙን በማስተላለፍ ርክክብ የማስፈጸም አገልግሎት የሚሰጥ የምርት ገበያው ክፍል ነው፡፡

   3.6. "የምርት ገበያው ክፍያ አስፈፃሚ ተቋም" ማለት የግብይቶችን ክፍያና ርክክብ የማስፈጸም አገልግሎት የሚሰጥና ስለምርት ገበያው ሆኖ ለአባላት የሚፈጸምን ክፍያ አስተማማኝ የሚያደርግ የምርት ገበያው ክፍል ወይም እንደ ክፍያ ሚፈጸሚያ ተቋም እውቅና የተሰጠው ሶስተኛ ወገን ነው፡፡

   3.7. "የክፍያ ሚፈጸሚያ ተቋም" ማለት በባለስልጣኑ እውቅና የተሰጠው ሆኖ የምርት ገበያው፣ የምርት ገበያው ክፍያ አስፈፃሚ ክፍል፣ የአገር ውስጥ ባንክ፣ ክፍያ ለማስፈጸም በምርት ገበያው የተሰየመ ባንክ ወይም ተመሳሳይ የፋይናንስ ተቋም ነው፡፡

   3.8. "ደንበኛ" ማለት አባል ግብይት የሚፈፅምለት ሰው ወይም አባሉ ለማገድ የግብይት ትዕዛዝ የሚቀበለው ሰው ነው፡፡

   3.9. "ምርት" ማለት ከሌላ ተመሳሳይ ምርት ጋር ማለዋወጥ የሚቻል ምርት ነው፡፡

   3.10. "የምርት ገበያ ንግድ" ማለት ለራስ ወይም ለሌሎች ጥቅም ሲባል በገበያው ንግድ የሚከሄደባቸውን ውሎች የግዥ ወይም የሽያጭ ትዕዛዞችን ሚፈላለግ ወይም መቀበል ነው፡፡

   3.11. "ውል" ማለት ለምርት ገበያ ግብይት ሲባል አንድን ምርት ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ወጥ ሆኖ የተዘጋጀና የምርቱን ማጠን፣ ዋጋ፣ ደረጃ፣ ውሉ ተፈጻሚ የሚሆንበትንና ርክክብ የሚፈጸምበትን ቀን በዝርዝር የሚያካትት ስምምነት ነው፡፡

   3.12. "በምርት ገበያው የተሰየመ መጋዘን" ማለት በምርት ገበያው የብቃት ሚረጋገጫ የተሰጠውና በሶስተኛ ወገን ባለቤትነት ይዞታ ሥር ያለ ወይም የሚሠራ ሕንፃና አዋሳኝ ቦታ ወይም ግቢ ሆኖ በመጋዘኑ አስተዳዳሪ ብቸኛ ቁጥጥር እየተደረገበት በምርት ገበያው ደንቦች መሠረት ምርቶች የሚከማቹበት ነው፡፡

3.13. "ኤሌክትሮኒክ የመጋዘን ደረሰኝ" ማለት በትዕዛዝ ሊተላለፍ የሚችል በምርት ገበያው በተሰየመ መጋዘን ማከማቻ ተቀባይነት ላገኙት ምርቶች ሕጋዊ የባለቤትነት መብት የሚሰጥ በምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ የሚታተም/የሚሰጥ የመጋዘን ደረሰኝ ነው፡

3.14. "ገበያ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 550/1999 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ነው፡

3.15. "የግብይት ፈጻሚ' ማለት ለሌሎች ወይም ለራሱ ሲል የምርት ግብይት ወሎችን በመግዛትና በመሸጥ ንግድ ሥራ የተሰማራ በባለሥልጣኑ እውቅና ያገኘ ማንኛውም ሰው ነው፡

3.16. "በምርት ገበያው የተሰየመ የክፍያ ባንክ" ማለት በምርት ገበያው ይሁንታ የተሰጠውና በባለሥልጣኑ እንደ ክፍያ ሚፈጸሚ ተቋም የታወቀ በግብይቱ ላይ የተፈጸሙ የአባል ግብይቶችን ክፍያ የሚፈፅም ባንክ ነው፡

3.17. "የምርት ገበያ አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አዋጅ ቁጥር 550/1999 እንደተሻሻለ ነው፡

3.18. "አባል" ማለት ለምርት ገበያ የሚጠየቀውን የአባልነት መመዘኛ የሚያሟላና በባለሥልጣኑ ዕውቅና የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው፡

3.19. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡

3.20. "የመጋዘን አገልግሎት ሰጪ' ማለት የምርት ገበያው ወይም በሚኒስቴሩ ወይም በሚኒስቴሩ ለዚሁ ዓላማ በተወከለ ተቆጣጣሪ አካል የተመዘገበ ሶስተኛ ወገን ነው፡

## ክፍል ሁለት

## ስለምርት ገበያው ሥራ መጀመር

1. ባለሥልጣኑ ከምርት ገበያው በሚቀርብለት ማመልከቻ መሠረት የምርት ገበያው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩትን መሥፈርቶች ማሟላቱን ካረጋገጠ የገበያውን ሥራ መጀመር በጽሁፍ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
2. በአንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ እንደ ሁኔታው ወደፊት የሚወጡ መሥፈርቶች እና ወዲያውኑ እና ወደፊት የሚፈጸሙ የምርት ገበያው ወሎችን ለማሥራትና ለመቆጣጠር የወጡ የምርት ገበያው ደንቦችን እና በአጠቃላይ የምርት ገበያውን ማቋቋሚ ደንቦችን በተለይም -
   1) የምርት ገበያውን ቦርድ፣ አወቃቀሩን እና የሥራ አመራሩን ሥልጣን እና ሥራውን የሚያከናውንበት ሥነ ሥርዓት የሚገልጽ፣
   2) የምርት ገበያውን ሥራ አመራር ሥልጣንና ተግባራት፣
   3) በተለያዩ ደረጃ የሚመድቡ አባላት ለምርት ገበያው አባልነት የሚመዘገበብትን፣ ከአባልነት የሚገለሉብትን፣ ለሚጡ የሚይችሉብትን፣ የሚሰናበቱብትን እና ወደ አባልነት ስለሚመለሱብት ሁኔታ፣
   4) በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት የሚመዘገበብትን ሁኔታ እና ሕጋዊ ወኪሎቻቸውን ስለሚሞጠብትና ስለሚሾሙብት ሥነ ሥርዓት የሚገልጹ ደንቦችን ቅጂዎች የያዘ መሆን አለበት፡፡
3. የምርት ገበያው ስለሥራው መጀመር ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ለማግኘትና በተሰጠው ፈቃድ መሠረት ለመቀጠል፣
   1) የሚቸውም ግብይት የሚፈረግባቸው ወሎች ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች እና ምርት ገበያው ወስጥ ከመግባት የሚከለክሉ ገደቦችን ጭምር ተፈፃሚነት ለሚረጋገጥ ቁጥጥር ሚድረግ፣
   2) ለአሳሳች ድርጊት ያልተጋለጡ የግብይት ወሎችን ብቻ በምርት ገበያው ላይ ማዘርዘር፣
   3) አሳሳች ድርጊት፣ ዋጋ ማዛባት፣ እና የርክክብ ሂደትን የሚያስተጓጉሉ ድርጊቶችን ለመካላከል የግብይት አሠራርን መከታተል፣
   4) አስፈላጊ እና ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ሊኖር የሚገባ የግብይት መጠን ገደብ ወይም ለሚደረግ ግብይት የሚኖር ተጠያቂነትን ለመወሰን የሚያስችል ደንብ ማዘጋጀት፣
   5) ከባለሥልጣኑ ጋር በመመካከርና በመተባበር አስፈላጊ ሲሆን እና እንደሁኔታው የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታን የሚመለከት ስልጣን የሚተገበርበትን ሁኔታ የሚመለከቱ ደንቦች በሥራ ላይ ማዋል፡፡
      አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና እንደሁኔታው ይህ ስልጣን የሚከተሉትን ያካትታል፡ -
      /ሀ/ በማንኛውም ወሎች ላይ ያልተፈጸሙ ግዴታዎችን የማዘወር ወይም የማቀረት፣
      /ለ/ በማንኛውም የግብይት ወሎች የተደረጉ ግብይቶችን የማቀረት ወይም የማገድ፣ እና
      /ሐ/ በማንኛውም የግብይት ወሎች ተሳታፊዎችን ልዩ የዋስትና ተቀማጭ ግዴታ እንዲያሟሉ የማጠየቅ፣
   6) ለባለስልጣኑ፣ ለግብይት ተሳታፊዎች እንዲሁም ለሕዝቡ -
      /ሀ/ የምርት ገበያ ወሎችን ይዘት፣
      /ለ/ በምርት ገበያው ወይም የምርት ገበያው በሚጠቀምባቸው መድረኮች ግብይት

የሚካሂደባቸውን ዘዴዎች፣ መረጃዎችን ማቅረብ፣

7) በምርት ገበያው ላይ ግብይት የሚፈጸምባቸውን ወሎች የየዕለት ዋጋ እና መጠን ይፋ ማድረግ፣
8) ተወዳዳሪ፣ ግልጽ እና ቀልጣፋ የግብይት መድረክ እና የግብይት ዘዴዎችን ማመቻቸት /ማቅረብ/፣
9) የምርት ገበያው ደንበኞችን ለመርዳትና በገበያው ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ጉዳት ለመከላከል ሲልና የምርት ገበያው ደንብ በመጣሱ ምክንያት ማስረጃ ለማቅረብ እንዲያስችለው ሲል የታወቁ የምርት መረጃዎችን የመመዝገብ፣ በአስተማማኝ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ የአሠራር ደንብና ሥነ ሥርዓት እንዲከበር የማድረግ፣
10) የማከማቻ መጋዘን ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን አጣርቶ ለማፅደቅ የሚረዱ ደንቦችን ማዘጋጀት እና ተፈፃሚ ማድረግ፣
11) በምርት ገበያው በተመዘገቡ የማከማቻ መጋዘኖች ምርቶችን ናሙና ለመውሰድ፣ ደረጃ ለማውጣት፣ ምርት ለመረከብ፣ እና ለማከማቸት የሚረዱ ደንቦችን ማውጣትና ማስፈጸም፣
12) የኤሌክትሮኒክስ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝን የሚመለከቱ ደንቦችን ማዘጋጀትና ተፈፃሚ ማድረግ፣
13) የማዕከላዊ ማከማቻ መጋዘኖችን አሠራር ደንብ ማውጣትና ማስፈጸም፣
14) የክፍያ ማጠቃለያ ተቋማትን አሠራር ለመወሰን የሚያስችል ደንብ ማውጣትና ማስፈጸም፣
15) የአባላትን፣ የአባላት ሕጋዊ ወኪልን የፋይናንስ አቋም ለማረጋገጥ እንዲሁም የደንበኞችን የዋስትና ተቀማጭ ለመከላከል የሚያስችል ደንብ ማውጣትና ማስፈጸም፣
16) የምርት ርክክብን የሚመለከቱ ደንቦችን ማውጣትና ማስፈጸም፣
17) የምርት ገበያ አባል ሕጋዊ ወኪል ሆኖ በሚሰራ ማንኛውም ወገን በሚፈጸም የማይገባ አሠራር ምክንያት በግብይት ተሳታፊዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል የሚያስችል ደንብ ማዘጋጀትና ማስፈጸም፣
18) ለግብይት ተሳታፊዎች አማራጭ የክርክር መፍቻ ስልቶችን ለማጠቀም የሚያስችሉ አመቺ የሆኑ ደንቦችን ማውጣትና ማስፈጸም እንዲሁም መድረኮችን ማመቻቸት /ማቅረብ/፣
19) ዳይሬክተሮችን፣ በአባላት የሚመረጡ የግልግል ዳኞችን፣ የምርት ገበያው አባላትን እና ሕጋዊ ወኪሎቻቸውን እንዲሁም ከምርት ገበያው ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው ሌላ ሰው ለማፅደቅ የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ ማስፈርት ማዘጋጀትና ማስፈጸም፣
20) በምርት ገበያው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የጥቅም ግጭት የሚያስከትሉ አሠራሮችን ለመቀነስና የጥቅም ግጭት ሲከሰትም ለመፍታት የሚያስችል ደንብ ማዘጋጀት እና ማስፈጸም፣
21) ከምርት ገበያው አሠራር ጋር የሚገናኙ ሰነዶችን በባለሥልጣኑ ተቀባይነት በሚኖረው ሁኔታ ለ10 አመታት ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡

4. ባለሥልጣኑ ገበያው በደንብና ባስቀመጣቸው መሥፈርቶች መሠረት መሥራቱን ለመመርመርና ለማረጋገጥ ገበያው ሥራውን ወደሚያከናውንበት ሥፍራ ለመግባት ይችላል፡፡
5. የምርት ገበያውን ሥራ መጀመር ስለመፍቀድ
    1) ባለሥልጣኑ የምርት ገበያው ሥራውን ለመጀመር ማመልከቻ ባቀረበ በ7 የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃድ መስጠት፣ ወይም የመከልከል ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ ሥራውን ለመጀመር የምርት ገበያው ያቀረበውን ጥያቄ ካልተቀበለ ጥያቄውን ያልተቀበለበትን ምክንያቶች መግለጽ አለበት፡፡ የምርት ገበያው ሥራውን ለመጀመር ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ካጣ ለባለሥልጣኑ አቤቱታ የማቅረብ እና የማስማት፣ በባለሥልጣኑ የተሰጠው ውሳኔ የማይስማማው ሆኖ ሲገኝም ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡
    2) ባለሥልጣኑ ሳይፈቅድ የምርት ገበያው አዳዲስ ሕጎችን ማውጣት ወይም ነባር ሕጎችን ማሻሻል አይችልም፡፡
    3) ባለሥልጣኑ ሳይፈቅድ የምርት ገበያው አዳዲስ የግብይት ወሎችን ማዘጋጀት ወይም ነባር የግብይት ወሎችን ማሻሻል አይችልም፡፡
    4) የምርት ገበያው ሥራ ለመጀመር ያቀረበው ማመልከቻ ስለሚፈቀዱ፣ አዳዲስ ሕጎችን፣ የምርት ግብይት ወሎችን ለማውጣት፣ ነባር ሕጎችን እና ወሎችን ለማሻሻል የቀረቡ ጥያቄዎች ስለሚፈቀዳቸው የተሰጡ ወሳኔዎች በታወቁ ጋዜጦች መታተም አለባቸው፡፡ እነዚህ ፈቃዶች በጋዜጣ ከታተሙበት ጊዜ ጀምሮ ሕጋዊ ወጤት ይኖራቸዋል፡፡
6. የምርት ገበያው ደንቦቹን፣ የሥራ ሁኔታዎችን ወይም የባለሥልጣኑን ማቋቋሚያ አዋጅ ድንጋጌዎች፣ መመሪያዎች ወይም ትዕዛዞች ካላከበረ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ባለሥልጣኑ ስላለው ስልጣን፡-
    1) የምርት ገበያው፣ ማናቸውም የምርት ገበያው ዳይሬክተር፣ የሥራ ኃላፊ፣ ወኪል ወይም ተቀጣሪ ሥራውን የሚመለከቱ ደንቦችን ካላከበረ ወይም ተፈፃሚ ካላደረገ ወይም የምርት ገበያው ወይም የምርት ገበያው ማናቸውም ዳይሬክተር፣ የሥራ ኃላፊ፣ ወኪል ወይም ተቀጣሪ የባለሥልጣኑን ማቋቋሚያ አዋጅ ወይም በባለሥልጣኑ የወጡ መመሪያዎችን ወይም ትዕዛዞችን ከጣሰ ባለሥልጣኑ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከአንድ በላይ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡
        /ሀ/ ባለሥልጣኑ የምርት ገበያውን፣
            (i) በምርት ገበያው መድረኮች ላይ የሚካሄዱትን ግብይቶች እንዲያግድ፣

(ii) የተወሰኑ የግብይት ወሎችን ወይም የተለዩ የምርት አይነቶች ላይ የሚከሄዱ ግብይቶችን እንዳያግድ፣

(iii) በምርት ገበያው የሚከሄድ ግብይት ያልተፈፀሙ ግዴታዎችን ማጠናቀቅ እንዲወሰን፣

(iv) በምርት ገበያ የተፈጸሙ ማንኛውም የግብይት ውሎች ወይም የተለዩ አይነት የግብይት ውሎች ወይም በተለዩ የምርት አይነቶች ላይ ስምምነት የተደረሰባቸውን ምርቶች የሚከረከቢያ ጊዜ እንዲያስተላልፍ ሊያዘው ይችላል፡፡

በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት እንዲፈፀሙ የሚተላለፉ ትዕዛዞች ከሚፀማቸውና አቤቱታ ከማቅረቡ በፊት እርምጃው እንዲወሰድ የተፈለገበት ምክንያት ከ7 ቀናት በፊት ለምርት ገበያው ቦርድ ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ በጽሁፍ ማድረስ አለበት፡፡

/ለ/ ምርት ገበያውን፣ የምርት ገበያውን ዳይሬክተር፣ የሥራ ኃላፊ፣ ወኪል፣ ሠራተኛ የምርት ገበየውን ደንብ ወይም መመሪያ ወይም ባለሥልጣኑ ያስተላለፈውን ትዕዛዝ እንዲያከብር ወይም እንዲያስፈጽም ማጠየቅ፣

/ሐ/ የምርት ገበያውን ወይም የሚሞላከተውን ግለሰብ ማሰፅ፣

/መ/ የምርት ገበያውን፣ የምርት ገበያውን ዳይሬክተር፣ የሥራ ኃላፊ፣ ወኪል፣ ሠራተኛ፣ ባለሥልጣኑ በሚያዘው መሠረት የደረሰውን የሕግ መጣስ ለመቀነስ ወይም ለማስተካከል የሚያስችሉ እርምጃዎች እንዲወሰድ ማጠየቅ፣

2) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 /ለ/ /ሐ/ እና /መ/ የተጠቀሱትን እርምጃዎች ለመውሰድ ማሰቡን ከ15 የሥራ ቀናት በፊት ለምርት ገበያው፣ ለምርት ገበያው ዳይሬክተር፣ ለሥራ ኃላፊ፣ ለወኪሉ ወይም ለሠራተኛው እርምጃ ሊወሰድ የሚባበትን ምክንያት ከሚገልጽ ማስታወቂያ ጋር ማጠት አለበት፡፡

7. **ባለሥልጣኑ እና የምርት ገበያው የዲስፒሊን እርምጃ ለመውሰድ ስላላቸው ሥልጣን**

1) የምርት ገበያው በምርት ገበያው ደንብ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ወይም በደንቡ የጊዜ ገደብ ላልተወሰነላቸው ጉዳዮች በህሊና ግምት በቂ በሚባል ጊዜ ውስጥ የዲስፕሊን እርምጃ ያልወሰደ እንደሆነ ባለስልጣኑ የምርት ገበያው ጉዳዩን መርምሮ እርምጃ በመውሰድ ወይም የተፈፀመ የህግ ጥሰት አለማግኘቱን በሚረጋገጥ እንዲያሳውቀው በጽሁፍ ትዕዛዝ ለሰጥ ወይም የራሱን ምርመራ አካሂዶ ማንኛውንም የምርት ገበያ አባል ሊያግድ፣ ከአባልነት ሊያስወግድ ወይም አግባብነት ያለው ሌላ የዲስፒሊን እርምጃ ሊወሰድ ወይም ማንኛውም ሰው በምርት ገበያው እንዳይሳተፍ ሊከለከል ይችላል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከተው እርምጃ የሚወሰደው በምርት ገበያው ደንቦች መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡

2) በምርት ገበያው ደንቦች የተካተተው ማናቸውም የዕገዳ፣ ከአባልነት የማስወገድ፣ የዲስፒሊን እርምጃ ወይም በምርት ገበያው ከመገልገል የመከልከል ሥነ ሥርዓት የእርምጃው ምክንያት ጭምር የተገለፀበት የጽሑፍ ማስታወቂያ ለባለሥልጣኑ እና ለታገደው፣ ለተወገደው፣ ሌላ የዲስፒሊን እርምጃ ለተወሰደበት ወይም በምርት ገበያው እንዳይገለገል ለተከለከለው ሰው በሠላሣ የሥራ ቀናት ውስጥ የሚሰጥበትን ሁኔታ ማዛዝ አለበት፡፡ የምርት ገበያው የደረሰበትን መደምደሚያ እና የወሰዳቸውን እርምጃዎች ወይም የተጣሉ ቅጣቶችን ጨምሮ ለወሰዳቸው እርምጃዎች ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡ ሆኖም ለወሳኔው መሠረት የሆኑ ማስረጃዎች የዕገዳ፣ የስንብት ወይም ሌላ የዲስፒሊን እርምጃ ለተወሰደበት ሰው ወይም በምርት ገበያው እንዳይገለገል ለተከለከለው ሰው ወይም ለባለሥልጣኑ ካልሆነ በስተቀር ለሌላ ሰው ይፋ ሊደረግ አይችልም፡፡

8. **በምርት ገበያው የተወሰዱ የዲስፒሊን እርምጃዎችን ለመመርመር ባለስልጣኑ ስላለው ሥልጣን**

1) የምርት ገበያው አንድ ሰው እንዲታገድ፣ እንዲወገድ፣ ሌላ የዲስፒሊን እርምጃ እንዲወሰድበት ወይም በምርት ገበያው እንዳይገለገል ያደረገበትን ውሳኔ ባለሥልጣኑ እንደሁኔታው ተገቢ ነው ባለው መመዘኛና ሥነ ሥርዓት ወይም ለዚሁ በተቀማጠ መመዘኛና ሥነ ሥርዓት መሠረት በድጋሚ ሊመለከት ይችላል፡፡ በተጨማሪም በምርት ገበያው ውሳኔ መብቱ ተነካ በሚል ሰው በሚቀርብለት አቤቱታ ማሻነት ወይም በራሱ አነሳሽነት ባለሥልጣኑ የተጠቀሰውን ውሳኔ በድጋሚ ሊያይ ይችላል፡፡

2) የምርት ገበያውን ውሳኔ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት በድጋሚ የሚያየው ባለሥልጣን የተሰጠው ውሳኔ በምርት ገበያው መርሆዎች /ሕጎች እና በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅና መመሪያዎች መሠረት ስለሚፈፀሙ ከሚመረ በኋላ ሊያፀናው፣ ሊያሻሽለው፣ ወድቅ ሊያደርገው ወይም በድጋሚ እንዲታይ ሊመልሰው ይችላል፡፡ በፌደራል ከፍተኛ

ፍ/ቤት በድጋሚ ሊታይ ማቻሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ስር የሚሰጠው ማንኛውም ትዕዛዝ በምርት ገበያው በሚሱ ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3) ባለሥልጣኑ ተገቢ ከማለው ጉዳዩ በድጋሚ እስኪታይ ድረስ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት የተወሰደውን እርምጃ እንዳይፈፀም ሊያግድ ይችላል፡፡

9. **ባለሥልጣኑ መደበኛ ሪፖርት እንዲቀርብለት ለመጠየቅ እና ቀጥተኛ ምርመራዎችን ለማድረግ ስላለው ስልጣን**

1) ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሠረት የምርት ገበያው እና አባላቱ ከሥራቸው ጋር የተያያዘ መደበኛ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፣

2) ከምርት ገበያው ወይም ከአባላቱ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ምርመራ በሚደረግበት ወቅት፣

/ሀ/ የምርት ገበያው እያንዳንዱ ዳይሬክተር፣ ሥራ አስኪያጅ፣ የሥራ ኃላፊ ወይም ተቀጣሪ፣

/ለ/ የምርት ገበያው እያንዳንዱ አባል፣

/ሐ/ የምርት ገበያው አባል ድርጅት ከሆነ እያንዳንዱ የድርጅቱ ሸሪክ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ፣ እና

/መ/ በ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ስር ከተጠቀሱት ሰዎች ጋር በንግድ ሂደት ግንኙነት የፈጠረ ማንኛውም ሌላ ሰው ወይም አካል፣

ከሚጣራው ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተያያዘ አግባብነት ያላቸውን የሂሣብ ማዛግብት፣ ማፃፎችን እና ሌሎች በእጁ ወይም በስሩ የሚገኙ ሰነዶችን ለባለሥልጣኑ የማቅረብ፣ እንዲሁም ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በተወሰነ ጊዜ ወስጥ ቃል ወይም መረጃ የማስጠት ግዴታ አለበት፡፡

10. የምርት ገበያው እና እያንዳንዱ አባል የሂሣብ ማዝገብና ባለሥልጣኑ የሚዘረዝራቸውን ሌሎች ሰነዶችን ማያዝ አለባቸው፡፡ የሚያዙት የሂሣብ ማዝገቦችና ሌሎች ሰነዶች በምርት ገበያው ከሆነ ከአሥር ዓመት ላልበለጠ ጊዜ፣ በአባላቱ ደግሞ ለአምስት ዓመታት ተጠበቀው መቆየት እና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ወስጥ በባለሥልጣኑ ምርመራ ይደረግባቸዋል፡፡

11. **የምርት ገበያው የሚከተሉትን መደበኛ ሪፖርቶች ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡**

**1) ዕለታዊ ሪፖርቶች**

የምርት ገበያው ለእያንዳንዱ የሥራ ቀን እያንዳንዱን የግብይት ውል ወይም የምርት ዓይነት በተመለከተ የሚከተሉትን ሚረጃዎች በተናጠል ማዛግቦ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

**/ሀ/** አጠቃላይ የግብይቱን ማጠን፣

**/ለ/** ለእያንዳንዱ ምርት ግብይት፣

(i) በጨረታ የቀረበውን ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ዋጋ፣ ለሽያጭ የቀረበበትን ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ዋጋ እንዲሁም የመከፈቻ፣ ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ እና ግብይቱ የተዘጋበትን ዋጋ፣

(ii) በመከፈቻና በመዝጊያ ጊዜ ምንም ግብይት ካልተካሄደ፣ የጨረታ ዋጋ ካልቀረበ ወይም ለሽያጭ የቀረበ ዋጋ ከሌለ የምርት ገበያው እንደሁኔታው በግብይቱ ሂደት የተገኘውን የመጀመሪያ ዋጋ /በመከፈቻው ዋጋ ምትክ/ ወይም የመጨረሻ ዋጋ /በመዝጊያው ዋጋ ምትክ/ የመጀመሪያና የመጨረሻ ዋጋ መሆኑን በግልጽ በማመልከት ይመዝግባል፡፡

/ሐ/ የዕለቱን የመዝጊያ ዋጋ እና የቀደመውን ቀን የመዝጊያ ዋጋ ንፅፅር፣

/መ/ ባለሥልጣኑ በሌላ ሁኔታ እንዲቀርብ ካልወሰነ በስተቀር የምርት ገበያው በንዑስ አንቀፅ 1 ስር የተጠቀሰውን ሚረጃ በሚከተለው ሚለኩ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

(i) የሚረጃውን የወረቀት ቅጂ /ሃርድ ኮፒ/ በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ ማቅረቡ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ በጽሐፍ ባፀደቀው ፎርማትና የዳታ ማስተላለፊያ ሥርዓት በማጠቀም፣

(ii) የተጠቀሱት የዳታ ዓይነቶች ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረቡ ሲሆን ሚረጃው ከሚያመለከተው ቀን ቀጥሎ ካለው የስራ ቀን 2.00 ሰዓት በፊት፡፡

/ሠ/ የምርት ገበያው ግብይት የተደረገባቸውን ዋጋዎች እና የግብይቱን ማጠን የሚያመለከት ሚረጃ በምርት ገበያው የማበያያ ሚድረክ ወዲያውኑ ለተሳታፊዎች ማቅረብ አለበት፡፡

/ረ/ የምርት ገበያው ከሚቀጥለው የንግድ ቀን 2.00 ሰዓት በፊት ስለእያንዳንዱ ምርት ግብይት ማጠን እና የመከፈቻ፣ ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ እና የተነገደበት የመዝጊያ ዋጋን የሚያመለከት የየዕለት ሚረጃ በቀላሉ ለሚረዳት እና ሊገኝ በሚችል ፎርም ያለክፍያ ለዜና ማናኛ እና ለሕዝብ ማቅረብ አለበት፡፡

2) ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመትና ዓመታዊ ሪፖርቶች

/ሀ/ የምርት ገበያው ግብይት የተደረገባቸውን ወሎች መጠን፣ ዋጋቸውን፣ የግብይቱን መጠን ከቀደመው ወር፣ ሩብ ዓመት ወይም ዓመት ጋር በማነፃፀር፣ በተለያዩ ዓይነት የግብይት ወሎች መካከል የንግዱን እንቅስቃሴ ስርጭት፣ ከምርት ገበያው ጋር በተያያዘ ወሳኝ የሆኑ በወሩ፣ በሩብ ዓመቱ እና በዓመቱ ወስጥ የደረሱ ክስተቶች እና በገበያው ላይ ስላሳደሩት ተፅዕኖ እንዲሁም የምርት ገበያው ቦርድ የተጠቀሰት ክስተቶች ሊያስከትሉ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመካላከል ያቀረበወን የምፍትሔ ሃሣብ ያካተተ ለእያንዳንዱ የግብይት ወል እና የምርት ዓይነት በተናጠል ሚዛን የያዘ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች ያደርጋል/ያቀርባል፡፡

/ለ/ የምርት ገበያው ዓመታዊ ሪፖርት የሂሣብ ማመዛዘኛ፣ ያለወን ሀብትና ያለበት ዕዳ መዝገብ እና ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫውን የያዘና በባለሥልጣኑ ዕውቅና ባገኘ ኦዲተር የተመረመረ እንዲሁም በምርት ገበያው ስለሚደረገው ግብይት ምጤ ሃብታዊ ትንተና የያዘ መሆን አለበት፡፡ የተጠቀሰው ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ አንድ ወር ጊዜ ወስጥ መቅረብ አለበት፡፡

12. ደንብ እንዲወጣ ወይም እንዲሻሻል ትዕዛዝ ለመስጠት ባለሥልጣኑ ስላለው ስልጣን

1) ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ወስጥ የምርት ገበያው ደንብ እንዲያወጣ ወይም የወጣውን ደንብ እንዲያሻሽል በጽሑፍ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2) በንዑስ አንቀፅ 1 ስር የተጠቀሰው ቢኖርም የምርት ገበያው ቦርድ በዚህ ክፍል ወስጥ የቀረበወን ደንብ የማውጣት ወይም ያለወን ደንብ የማሻሻል ትዕዛዝ ከተቃወመ ትዕዛዙ በተሰጠ ሠላሳ የሥራ ቀናት ወስጥ ባለሥልጣኑ ጉዳዩን በድጋሚ እንዲያጠነው ሊያመለክት ይችላል፡፡

13. የምርት ገበያው ደንብ የማውጣት ስልጣን

1) ከባለሥልጣኑ በቅድሚያ ይሁንታ ማግኘቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የምርት ገበያው የሚያደርገውን ግብይት ለመቆጣጠር የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2) በንዑስ አንቀፅ 1 ስር የተቀመጠው ጥቅል ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የሚወጣው መመሪያ በተለይም፦-

/ሀ/ አባልነትን፣

/ለ/ ግብይትን፣

/ሐ/ የምርት ገበያውን መከፈት፣ መዘጋትና የግብይቱን ሰዓት ስለመቆጣጠር፣

/መ/ ክፍያ ለፈፀምባቸው የሚገባ ወይም ያልተከፈለ ቀሪ ገንዘብ በክፍያ ሚፈፀሚያ ተቋም በኩል ለክፈልባቸው የሚችል የግብይት ወሎች ቁጥርና ዓይነት፣

/ሠ/ ከግብይት ወሎች ጋር የተያያዙ ርክክቦችና በልዩነት የሚሄዱ ክፍያዎችን በየጊዜው ለሚፈጸም ስለሚረዱ የክፍያ ሚፈጸሚያ ተቋምና በምርት ገበያው ስለተሰየሙ የርክክብ ባንኮች፣ ምርቶችን ስለማስረከብና የክፍያ አፈጻጸም፣ ስለማስረከቢያ ትዕዛዞች እንዲሁም የተጠቀሰት የክፍያ ሚፈጸሚያ ተቋም እና በምርት ገበያው የተሰየሙ የርክክብ ባንኮች ላይ ቁጥጥር ስለሚደረግበት ሁኔታ፣

/ረ/ የክፍያውን ቀን ስለመወሰን፣ ስለመቀየር ወይም ስለማስተላለፍ፣

/ሰ/ የምርቶቹን የመከፈቻ፣ የመዝጊያ፣ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ዋጋ ጨምሮ የገበያ ዋጋ መወሰን እና ይፋ ማድረግ፣

/ሸ/ እንዳስፈላጊነቱ የተወሰነ ገንዘብ በቅድሚያ ተቀማጭ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ማሟያዎች ካሉ እና ከዚህ ጋር የሚያያዙ ሌሎች ሁኔታዎች እና በጽሑፍ መሆን የሚገባቸውን የግብይት ወሎች ፎርማት ያካተተ የግብይት ወሎች ይዘት፣

/ቀ/ አባላትና ደንበኞቻቸው በመካከላቸው የሚያደርጓቸውን ስምምነቶች እንዲሁም ግዴታን አለመወጣት ወይም፣ የሻጭ ወይም የገዢ ወይም የአባል መክሰር የሚያስከትላቸውን ወጤቶች ስለመቆጣጠር፣

/በ/ የተወሰነ ደረጃ ያላቸው ወይም የተወሰኑ ዓይነት ምርቶች ወይም የምርት ገበያው አባላት በምርቶች ላይ የሚከናወኗቸው ስምምነቶች ተቀባይነት ሊያገኙ ስለሚችሉበት ወይም ስለሚከለከሉበት ሁኔታ፣

/ተ/ የግልግል ዳኝነትን ጨምሮ አለመግባባት ወይም መጣቶች የሚፈቱባቸውን መንገዶችና ሥነ ሥርዓት፣

/ቸ/ የአገልግሎት ክፍያ፣ ወጪ እና መቀጮ የሚወሰንበት እና የሚከፍልበትን፣

/ነ/ በማንኛውም ችሎታ ወል ወስጥ ስለሚገቡ ወገኖች የግብይት ሂደት ቁጥጥር፣

/ኘ/ የዋጋና የክፍያ መጠን መዋዠቅን ስለመቆጣጠር፣

/ኀ/ ከፍተኛና ዝቅተኛ ዋጋን የመወሰን ሥልጣንን ጨምሮ ለክስተት ስለሚችል የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ እና በዚህ ጊዜ ሊሰራበት ስለሚችል ስልጣን፣

/አ/ አባላት በራሳቸው ስም ስለሚያደርጉት ግብይት ቁጥጥር፣

/ከ/ እያንዳንዱ አባል የሚያካሂደውን ግብይት መጠን በተመለከተ ስለተቀመጡ ገደቦች፣ እና

/ኸ/ የምርት ገበያው ቦርድ በሚቀርበው ጥያቄ አባላት ያካሄዱትን ግብይት በተመለከተ ሚጃ፣ ማብራሪያ እና የሂሣብ መዝገብ ለማቅረብ ስላለባቸው ግዴታ፣ ያካተተ ሊሆን ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወጣው ደንብ፣

/ሀ/ ባለመክበራቸው ምክንያት የተገባባቸውን የግብይት ውሎች ዋጋ የሚያሳጡ መመሪያዎች ወይም ደንቦችን መግለፅ፣

/ለ/ ባለመክበራቸው ምክንያት የተገባባቸውን የግብይት ውሎች ሕገወጥ የሚያደርጉ መመሪያዎችና ደንቦችን መግለጽ፣

/ሐ/ ማንኛውንም ደንብ መተላለፍ

(i) የሚመለከተውን አባል የገንዘብ መቀጮ የመክፈል ኃላፊነት፣ ወይም

(ii) የሚመለከተው አባል ከምርት ገበያው አባልነት እንዲወገድ ወይም እንዲታገድ ሊያስደርግ ወይም ከገንዘብ መቀጮ ውጪ ያሉ ተመሳሳይ ቅጣቶችን ሊያስከትልበት እንደሚችል፣ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀፅ ስር የሚወጣ ማንኛውም ደንብ በባለሥልጣኑ ከጸደቀ በኋላ ታትሞ መውጣት አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ ለግብይቱ ወይም ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በጽሑፍ በሚሰጥ ትዕዛዝ የደንቡን ታትሞ መውጣት ሊያስቀር ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለክፍያ ሚፈፀሚ ተቋማት ተግባራትና ዕውቅና

1. የምርት ገበያው በክፍያ ሚፈፀሚ ተቋሙ ወይም በምርት ገበያው በተሰየሙ የርክክብ ባንኮች ወይም በሌላ በባለሥልጣኑ ዕውቅና በተሰጠው የክፍያ ሚፈፀሚ ተቋም አማካኝነት የሁሉንም ግብይቶች ክፍያና ርክክብ ይፈፅማል፡፡

**2. የምርት ገበያው የክፍያ ሚፈፀሚ ተቋም ተግባራት**

የምርት ገበያው የክፍያ ሚፈፀሚ ተቋም ተግባር የግብይቱን ክፍያና ርክክብ እና የተለያዩ ወገኖችን የአደጋ ቁጥጥር አስተዳደር /ሪስክ ሜጅመንት/ ሂደት ሚደራጀትና ማስተዳደርን የሚጠቃልል ሆኖ በተለይም፣

1) የምርት ገበያው አባል ከግብይቱ የሚመነጩ ግዴታዎችን በወቅቱ የመወጣት ችሎታውን በተመለከተ የገንዘብ አቋሙን የመቆጣጠር፣

2) ተዛማጅ ግብይቶችን ማስታረቅ እና አባላት ላለባቸው የተጣራ ዕዳ እንደተቃራኒ ወገን ሆኖ ሚፈፀም፣

3) የተዛማጅ ግብይቶችን ርክክብ በምርት ገበያው በተሰየሙ የርክክብ ባንኮች በኩል ለማካሄድ ማስማማትን ያካትታል፡፡

4) የአገናኝና የወስን አገናኝ አባላት ደንበኞች ሽያጭ የተጣራ ክፍያ በምርት ገበያው ለተሰየሙ ባንኮች በሚያስተላልፈው የክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ለእያንዳንዱ ደንበኛ መድረሱን ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪም ደንበኞች ግዥ ለሚፈፀም የሚያስገቡት ገንዘብ ለራሳቸው ግብይት ሚፈፀሚ ብቻ መዋሉን፣ ግዢ ሳይፈፀም ቀርቶ ገንዘቡን ሚልሰ ለማውጣት ሲያስፈልግ ደግሞ አገናኝ ወይም ወስን አገናኝ አባሉ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት በቀጥታ ለደንበኛው መድረሱን ያረጋግጣል፡፡ ዝርዝሩ በገበያው የወስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡

**3. በምርት ገበያው የተሰየሙ የርክክብ ባንኮች ተግባራት**

በምርት ገበያው የተሰየሙ የርክክብ ባንኮች ተግባር በምርት ገበያው የተከናወኑ ግብይቶችን ርክክብ ማመቻቸትን የሚያጠቃልል እና በተለይም፣

1) አባላት በመካከላቸው ካደረጓቸው ግብይቶች ጋር በተያያዘ በአባላት የባንክ ሂሣብ ወስጥ ገንዘብ የሚሰበሰብበትን ሁኔታ የማመቻቸት፣

2) ከምርት ገበያው የክፍያ ሚፈፀሚ ተቋም በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በርክክብ ወቅት ገንዘብ ማዛወር፣

3) የአባላት የባንክ ሂሣብ ስላለበት ደረጃ ከምርት ገበያው ጋር ሚጃ መቀያየርን /ማራትን/ ያካትታል፡፡

**4. ስለምርት ገበያው የክፍያ ሚፈፀሚ ተቋም የዕውቅና ማመልከቻ**

የምርት ገበያው የክፍያ ሚፈፀሚ ተቋም ዕውቅና ለማግኘት ለባለሥልጣኑ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡ የሚቀርበው ማመልከቻ በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 25 ስር የተቀመጡትን ዕውቅና ለማግኘት መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች እንደሚያከብርና በማክበሩ እንደሚቀጥል የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

**5. የማመልከቻ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት**

1) የምርት ገበያው የክፍያ ሚፈፀሚ ተቋም ዕውቅና ለማግኘት ለባለሥልጣኑ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

2) የሚቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡፡

/ሀ/ በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 2/1/ ስለ ክፍያ ሚፀሚያ ተቋም በተሰጠው ትርጉም መሠረት እንደሚሰራ የሚገልጽ ቃል፣

/ለ/ የምርት ገበያው የክፍያ ሚፀሚያ ተቋም ደንቦች ቅጂ፣

/ሐ/ የምርት ገበያው የክፍያ ሚፀሚያ ተቋም በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 25 የተቀመጡትን እያንዳንዱን ማስፈርት እንዴት ሊያሟሉ እንደሚችሉ የሚያሳይ ማብራሪያ፣

/መ/ የምርት ገበያው የክፍያ ሚፀሚያ ተቋም በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 25 ስር የተሰጠቀሱትን ማስፈርቶች ለማሟላት እንዲችል በምርት ገበያው ከተሰየሙ የርክክብ ባንኮች ጋር ያደረጋቸውን ወይም የሚያደርጋቸውን ስምምነቶች መግለጽ፣ ስምምነቶቹ የሚሰጡዋን አገልግሎት ለይተው ማስቀመጥ ይገባቸዋል፡፡ ስምምነቱ የሚጬረሻ ካልሆነና ገና ያልተተገበረ ከሆነ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አገልግሎቱ እንደሚሰጥ የሚያሳይ ሚረጋገጫ

/ሠ/ አመልካች በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 25 ስር የተገለፁትን ማስፈርቶች ማሟላት የሚያስችለው የአሰራር ሥርዓቱ የሚተሽበት ሥነ ሥርዓት፣ የተከናወኑ ፍተሻዎች ወይም የፍተሻ ውጤቶች ማብራሪያ፣

/ረ/ አመልካቹ በበቂ ዝርዝር በማመልከቻው ውስጥ ያካተተው ሚረጃ ሚስጥር እንደሆነ በመግለፅ በሚስጥር እንዲያዝለት ከጠየቀ ጥያቄውን ያቀረበበት ፅሁፍና የሚገፈውን ማስረጃ፡፡

## 6. ማመልከቻው የሚታይበት ጊዜ

1) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተቀመጠው ልዩ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደምርት ገበያው የክፍያ ሚጸሚያ ተቋም እውቅና ለማግኘት የቀረበውን አቤቱታ ማመልከቻው በቀረበ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑ መመርመር አለበት፡፡ ባለስልጣኑ ማመልከቻውን ተቀብሎ ዕውቅና ሊሰጥ ወይም ወድቅ ሊያደርግ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የተወሰኑ ሁኔታዎችን መሟላት በቅድመ ሁኔታነት አስቀምጦ ለምርት ገበያው የክፍያ ሚፀሚያ ተቋም ዕውቅና ሊሰጥ ይችላል፡፡ ባለስልጣኑ የምርት ገበያው የክፍያ ሚፀሚያ ተቋም ማመልከቻ ያልተሟላ መሆኑን እና የሚታይበትን ጉድለት ከገለፀ ማመልከቻው የሚታይበት ጊዜ ማመልከቻው ተሟልቶ እስኪቀርብ ከመቆጠር ታግዶ ይቆያል፡፡
2) ለምርት ገበያው የክፍያ ሚፀሚያ ተቋም ባለሥልጣኑ በተፋጠነ ሁኔታ ጊዜያዊ ዕውቅና ሊሰጥ ይችላል፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ የሚሰጠው ጊዜያዊ ዕውቅና የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎችና ባለስልጣኑ የሚያስቀምጠው የማብቂያ የጊዜ ገደብ ሊኖረው ይችላል፡፡
3) የምርት ገበያው የክፍያ ሚጸሚያ ተቋም ዕውቅና ለማግኘት የሚስችሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ የተሰጠው ጊዜያዊ ዕውቅና ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ቋሚ ዕውቅና ለማግኘት ማመልከት አለበት፡፡

## 7. በምርት ገበያው የተሰየመ የርክክብ ባንክ ዕውቅና ለማግኘት ስለሚያመለክትበት ሁኔታ

በምርት ገበያው የተሰየመው የርክክብ ባንክ በክፍያ ተቋምነት ዕውቅና ለማግኘት ማመልከቻ ማቅረብ እና በማመልከቻውም በገበያው ስለተሰየሙ የክፍያ ተቋማት የተቀመጡትን መሥፈርቶችና ሁኔታዎች እንደሚያከብርና ማክበሩን እንደሚቀጥል መግለጽ አለበት፡፡

## 8. በምርት ገበያው እንደተሰየመ የርክክብ ባንክ ዕውቅና ለማግኘት የሚቀርበው ማመልከቻ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት

1) በምርት ገበያው የተሰየመው የርክክብ ባንክ ከባለሥልጣኑ ዕውቅና ለማግኘት ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡
2) የሚቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፣
   /ሀ/ አመልካች ከምርት ገበያው ጋር ቁርኝት በመፍጠር እንዴት ማስራት እንዳሰበ የሚያሳይ ዝርዝር ሀሳብ፣
   /ለ/ በምርት ገበያው የተሰየመው ባንክ በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 2/1/ ስለክፍያ ሚጸሚያ ተቋም በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት ሥራውን የሚያከናውን መሆኑን የሚገልጽ ቃል፣
   /ሐ/ በምርት ገበያው የተሰየመው የርክክብ ባንክ ከምርት ግብይት ርክክብ ጋር በተያያዘ ያሉትን ደንቦች ቅጂ፣
   /መ/ በምርት ገበያው የተሰየመው የርክክብ ባንክ በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 25 የተቀመጡትን እያንዳንዱን ማስፈርት እንዴት ማሟላት እንደሚችል የሚያመለክት ማብራሪያ፣
   /ሠ/ በምርት ገበያው የተሰየመው የርክክብ ባንክ በባለሥልጣኑ አዋጅ አንቀፅ 25 የተጠቀሱትን ማስፈርቶች ለማሟላት እንዲችል ከምርት ገበያው ጋር ያደረጋቸውን ወይም የሚያደርጋቸውን ስምምነቶች መግለፅ አለበት፡፡ ስምምነቶቹ የሚሰጡዋን አገልግሎት ለይተው ማስቀመጥ ይገባቸዋል፡፡ ስምምነቱ የሚጬረሻ

ካልሆነና ገና ያለተተገበረ ከሆነ ለሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አገልግሎቱ እንደሚሰጥ የሚያሳይ ማረጋገጫ

/ረ/ አመልካቹ በባለስልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 25 ስር የተለገጹትን ማስፈርቶች ማሟላት የሚያስችለው የአሰራር ስርዓቱን የሚቲትሽበት ስነ ስርዓት፣ የተከናወኑ ፍተሻዎችና የፍተሻ ወጤቶቹ ማበራሪያ፣

/ሰ/ አመልካቹ በበቂ ዝርዝር በማመልከቻው ወስጥ ያካተተው መረጃ ሚስጥር እንደሆነ በመግለፅ በሚስጥር እንዲጠበቅለት ከጠየቀ የሚደግፈወን ማስረጃ፡፡

## 9. ማመልከቻው የሚታይበት ጊዜ

1) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የቀማጠው ልዩ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ በምርት ገበያው የተሰየመው የርክክብ ባንክ ዕወቅና ለማገኘት ያቀረበወን አቤቱታ ማመልከቻው በቀረበ በሰባት የሥራ ቀናት ወስጥ ባለሥልጣኑ መመርመር አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ ማመልከቻወን ተቀብሎ ዕወቅና ሊሰጥ ወይም ወድቅ ሊያደርግ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የተወሰኑ ሁኔታዎችን መሟላት በቅድመ ሁኔታነት አስቀምጦ በምርት ገበያው በተሰየመው የርክክብ ባንክ ዕወቅና ሊሰጥ ይችላል፡፡ በምርት ገበያው የተሰየመው የርክክብ ባንክ ማመልከቻ ያልተሟላ መሆኑን እና የሚታይበትን ጉደለት ባለሥልጣኑ ከገለፀ ማመልከቻው የሚታይበት ጊዜ ማመልከቻው ተሟልቶ በድጋሚ እስኪቀርብ ከመቆጠር ታግዶ ይቆያል፡፡

2) በምርት ገበያው ለተሰየመው የርክክብ ባንክ ባለሥልጣኑ በተፋጠነ ሁኔታ ጊዜያዊ ዕወቅና ሊሰጥ ይችላል፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ባለስልጣኑ ለሚሰጠው ጊዜያዊ ዕወቅና ቅድመ ሁኔታዎችና የጊዜ ገደብ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

3) በምርት ገበያው የተሰየመው ባንክ እንዲያሟላ የተቀማጡለትን ሁኔታዎች ሲያሟላ የጊዜ ገደቡ ከማበቃቱ በፊት ቋሚ ዕወቅና ለማገኘት ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

## 10. የክፍያ ሚፀሚያ ተቋም ያቀረበወን የዕወቅና ጥያቄ ስለማፈግ

ባለስልጣኑ የቀረበለትን የዕወቅና ጥያቄ ካልተቀበለ ያልተቀበለበትን ምክንያት መግለጽ አለበት፡፡ ጥያቄው ተቀባይነት ካላገኘ ዕወቅና ለማገኘት ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛወም ሰው በባለስልጣኑ ፊት አቤቱታ የማቅረብና የማሰማት ዕድል ሊሰጠው እና በዚህ ደረጃ በሚሰጠው ወሳኔ የማይስማማ ከሆነ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችልበትን ሁኔታ ያካተተ ይሆናል፡፡

## 11. የክፍያ ሚፀሚያ ተቋም ዕወቅና ማታገድ ወይም ማነሳት

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሁኔታዎች ማከሰታቸወን ካረጋገጠ ለክፍያ ሚፀሚያ ተቋም የሰጠወን ዕወቅና ከሠላሳ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ለማገድ ወይም ለማንሳት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

1) የክፍያ ሚፀሚያ ተቋም ዕወቅና ለማገኘት በቅድመ ሁኔታነት በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 25 ስር የተቀማጡትን ማስፈርቶች ተግባራዊ ካላደረገ ወይም የራሱን አሰራሮች፣ ማስፈርቶች እና ሥነ ሥርዓቶች ተፈፃሚ ካላደረገ፣ ወይም

2) የክፍያ ሚፀሚያ ተቋሙ ወይም የክፍያ ሚጸሚያ ተቋም ማንኛወም ዳይሬክተር፣ የሥራ ኃላፊ፣ ወኪል ወይም ተቀጣሪ የባለሥልጣኑን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 25 ማንኛወንም ድንጋጌ ወይም የባለሥልጣኑን ማንኛወንም መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ከተላለፈ ወይም እየተላለፈ ከሆነ፡፡

## 12. የማሰማት እና የይግባኝ መብት

1) በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 26 መሠረት እወቅና ሲነፈግ፣ የተሰጠው ዕወቅና ሲታገድ ወይም ሲሻር ዕወቅናወን ለማገኘት ያመለከተወና ዕወቅና የተነፈገው፣ የታገደበት ወይም የተሻረበት ሰው ቅሬታው በባለሥልጣኑ ዘንድ እንዲታይለትና እንዲሰማለት፣ ይህንኑ ተከትሎ የተሰጠዉም ወሳኔ የሚጐዳው ከሆነ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

2) በባለሥልጣኑ ፊት የሚሰጠው ቃል ወይም የሚቀርበው ማስረጃ በመመሪያዎቹ መሠረት በአግባቡ ተመዝግቦ ይቀመጣል፡፡ በዚህ መልክ የተያዘው መዝገብ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በሚያይበት ጊዜ በማስረጃነት ይታያል፡፡

3) የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባለሥልጣኑ የሰጠወን ትእዛዝ ሊያፀና ወይም ሊሽር ወይም ትዕዛዙን እንዲያሻሽል መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ባለሥልጣኑ የሰጠው ትዕዛዝ በማስረጃ ያልተደገፈ ወይም አግባብነት ያለው ማስታወቂያ ሳይሰጥ ወይም ተገቢ የሆነ የማሰማት ዕድል ሳይሰጥ የተሰጠ መሆኑን የክፍያ ሚፀሚያ ተቋሙ ካላሳየ በስተቀር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባለሥልጣኑ የሰጠወን ትዕዛዝ ሊያሻሽል ወይም ወድቅ ሊያደርግ አይችልም፡፡

## 13. ዕወቅና ለማገኘት የቀረበ አቤቱታን ስለመተው

ዕውቅና ለማግኘት የቀረበ አቤቱታ ለባለሥልጣኑ በማመልከት ሊቀርብ ይችላል፡፡ ከአመልካቹ ድርጊት፣ እንቅስቃሴዎች ወይም የዕውቅና አቤቱታው በባለሥልጣኑ ጋር እየታየ ባለበት ወቅት ከተከሰቱ ነገሮች ጋር በተያያዘ በባለሥልጣኑ የተወሰደ ወይም ሊወሰድ የሚችል እርምጃን የቀረበው የምዝገባ ጥያቄን የማንሳት አቤቱታ አያስቀረውም፡፡

**14. የክፍያ ሚዒፀሚ ተቋምን መተዳደሪያ ደንብ ወይም የግብይት ደንቦችን ማሻሻያ ለማፅደቅ ባለሥልጣኑ ስላለው ሥልጣን**

1) የክፍያ ሚዒፀሚ ተቋሙ

/ሀ/ እንደ ክፍያ ሚዒፀሚ ተቋም በሚያከናወነው ሥራ ላይ ተፅዕኖ ሊኖረው የሚችል የመተዳደሪያ ደንብ ማናቸውም ማሻሻያ ለማድረግ፣

/ለ/ እንደ ክፍያ ሚዒፀሚ ተቋም በሚያከናወነው ሥራ ላይ ተፅዕኖ ሊኖረው የሚችል የማንኛውም የንግድ ደንብ ለማውጣት፣

/ሐ/ እንደ ክፍያ ሚዒፀሚ ተቋም በሚያከናወነው ሥራ ላይ ተፅዕኖ ሊኖረው የሚችል የማንኛውም በሥራ ላይ ያለ የንግድ ደንብ ማሻሻያ ለማድረግ ሃሣብ ካለው በሚቻለው ጊዜ ወስጥ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ለባለሥልጣኑ የጽሑፍ ማስታወቂያ ማስጠት አለበት፡፡

2) የጽሑፍ ማስታወቂያው፡-

/ሀ/ የታሰበውን ማሻሻያ ወይም የንግድ ደንብ ሰነድ፣

/ለ/ የቀረበው ማሻሻያ ወይም ደንቡ በሥራ ላይ እንዲውል የታሰበበትን ቀን የሚገልጽ፣ እና

/ሐ/ የቀረበውን ማሻሻያ ወይም ደንብ ዓላማ ማብራሪያ ያካተተ መሆን አለበት፡፡

3) ባለሥልጣኑ በሠላሳ ቀናት ወስጥ ወይም ከክፍያ ሚዒፀሚ ተቋሙ ጋር በተስማሙበት ጊዜ ወስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በቀረበለት የማሻሻያ ሃሳብ ወይም ረቂቅ ደንብ ላይ የሚሰጠውን ወሳኔ ለክፍያ ሚጸሚ ተቋሙ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

4) የቀረበውን የማሻሻያ ሃሣብ ወይም ደንብ ባለሥልጣኑ ካላፀደቀው/ ካልተቀበለው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 6 ስር በሚሰጠው ማስታወቂያ ይህንን ሁኔታ ለይቶ ማስቀመጥ ወይም ማመልከት አለበት፡፡

5) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ስር ከተሰጠው ስልጣን በተጨማሪ ለክፍያ ሚፀሚ ተቋሙ የጽሑፍ ማስታወቂያ በማስጠት የክፍያ ሚዒፀሚ ተቋሙን መተዳደሪያ ደንብ ወይም ሌሎች ደንቦችን ለማሻሻል ይችላል፡፡

6) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5 ስር ባለሥለጣኑ ለክፍያ ሚፀሚ ተቋም የሚሰጠው ማስታወቂያ፡-

/ሀ/ በባለሥልጣኑ የተደረገው ማሻሻያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልበትን መንገድ የሚያሳከት ድንጋጌን፣

/ለ/ ማሻሻያው ተግባራዊ የሚደረግበትን ቀን ማካተት አለበት፡፡

7) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5 ስር የተሰጠውን ማስታወቂያ የክፍያ ሚፀሚ ተቋሙ የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

**15. ባለሥልጣኑ የራሱን ደንቦች፣ ዕውቅና ለማግኘት እንደቅድመ ሁኔታ በባለሥልጣኑ ሚቋቋሚ አዋጅ ድንጋጌዎች የተቀመጡትን ማስፈርቶች፣ የባለሥልጣኑን መመሪያዎች ወይም ትዕዛዞች ባለከበረ የክፍያ ሚዒፀሚ ተቋም ላይ እርምጃ ለመውሰድ ስላለው ስልጣን**

1) የክፍያ ሚዒፀሚ ተቋሙ ማንኛውም የክፍያ ሚዒፀሚ ተቋሙ ዳይሬክተር፣ የሥራ ኃላፊ፣ ወኪል ወይም ሠራተኛ ስራውን የሚያሳከቱ ደንቦች፣ ወይም ዕውቅና ለማግኘት በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጡ ማስፈርቶችን ካላከበረ ወይም ተፈፃሚ ካላደረገ ወይም የክፍያ ሚዒፀሚ ተቋሙ ወይም ክፍያ ሚዒፀሚ ተቋሙ ማናቸውም ዳይሬክተር፣ የሥራ ኃላፊ፣ ወኪል ወይም ተቀጣሪ የባለሥልጣኑን ሚቋቋሚ አዋጅ ወይም በባለሥልጣኑ የወጡ መመሪያዎችን ወይም ትዕዛዞችን ከጣሰ/ከተላለፈ ባለስልጣኑ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡

/ሀ/ የክፍያ ሚዒፀሚ ተቋሙ ከምርት ገበያው ጋር በተያያዘ የሚያደርጋቸውን የሥራ/ የንግድ እንቅስቃሴዎች እንዲያግድ መመሪያ ማስጠት፣ በዚህ ንዑስ አንቀፅ መሠረት መመሪያ የሚሰጠው የእርምጃውን ምክንያት የሚገልፅ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለክፍያ ሚዒፀሚው ተቋም ቦርድ ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ከታሰበው እርምጃ ቢያንስ ሰባት የሥራ ቀናት በፊት ከተሰጠና ከተሰማ በኋላ ብቻ መሆን አለበት፡፡

/ለ/ የክፍያ ሚዒፀሚ ተቋሙ የክፍያ ሚዒፀሚ ተቋሙ ማናቸውም ዳይሬክተር፣ የሥራ ኃላፊ፣ ወኪል ወይም ሠራተኛ እንደ ጉዳዩ ሁኔታ የክፍያ ሚዒፀሚ ተቋሙን ደንቦች ወይም የባለሥልጣኑን መመሪያዎች ወይም ትዕዛዞች ባከበረ ሁኔታ ወይም ለማስፈፀም በሚያስችል ሚልኩ እንዲንቀሳቀሱ ማዘዝ፣

/ሐ/ የክፍያ ሚዒፀሚ ተቋሙን ወይም የሚያሳከተውን ግለሰብ ማገስጽ፣

/መ/ የክፍያ ሚፀሚ ተቋሙ የሚሚከተው ዳይሬክተር፣ የሥራ ኃላፊ፣ ወኪል ወይም ሠራተኛ የመተላለፉን ወጤት ለማስተካከል ወይም ለማቅለል በባለሥልጣኑ ትዕዛዝ የተሰጠባቸው እርምጃዎች እንዲወስዱ ማጠየቅ፣

2) ባለሥልጣኑ በንዑስ አንቀፅ 1 /ለ/፣ /ሐ/ እና /መ/ ስር የተጠቀሱትን እርምጃዎች በመወሰድ ሚበዑን ቢያንስ እርምጃዎቹን ከመወሰዱ አሥራ አምስት የሥራ ቀናት በፊት የእርምጃዎቹን ምክንያት ጭምር በሚገልፅ ማስታወቂያ ለክፍያ ሚፀሚ ተቋሙ ለሚሚከተው ዳይሬክተር፣ የሥራ ኃላፊ፣ ወኪል ወይም ሠራተኛ ማሳወቅ አለበት፡፡

**16. ዕወቅናው እንዲቋረጥ ስለማጠየቅ**

ዕወቅና የተሰጠው የክፍያ ሚፀሚ ተቋም የተሰጠው ዕወቅና በባለሥልጣኑ ሚቋቋሚ አዋጅ አንቀጽ 24 መሠረት እንዲቋረጥ/ እንዲያበቃ ለባለሥልጣኑ ማሜልከት ይችላል፡፡ የዕወቅናው መቋረጥ ማሜልከቻው በቀረበበት ጊዜ የተከሰቱ ማኘቸወም ድርጊቶች፣ እንቅስቃሴዎች ወይም ሁኔታዎች ባለሥልጣኑ የሚወስደውን እርምጃ ወይም ወደፊት እርምጃ እንዳይወስድ የማገድ ወጤት የላቸውም፡፡

**17. የክፍያ ሚፀሚ ተቋሙ መዛገቦችን ማያዝና ለባለሥልጣኑ በሚከተለው ሁኔታ መደበኛ ሪፖርቶች ማቅረብ አለበት፣**

1) የምርት ገበያው የክፍያ ሚፀሚ ተቋም በርሱ በኩል የተካሄዱ ግብይቶችን የሚስታረቅ ሥራዎችን እና ርክክብ የፀደቀላቸውን ግብይቶች የሚያመለክት ወርሃዊ ሪፖርት፣ እና

2) የራሳቸው ወይም የደንበኞቻቸው የሆነውን የአባላት ገንዘብ የተረከበ በምርት ገበያው የተሰየመ እያንዳንዱ የርክክብ ባንክ ገንዘብ የተረከበባቸውን ቀናት፣ የአስቀሚጩን ማንነት፣ ገንዘቡ በዕዳ የተመዘገበበትን፣ የወጣበትን ወይም በሌላ መንገድ የተወገደበትን ቀናት፣ እንዲሁም ገንዘቡ በእዳ ስለተመዘገበበት፣ ስለወጣበት ወይም ክፍያ ስለተፈጸማበት ሁኔታ እና የተጠቀሱትን ተግባራት ለሚፈጸም ስለተሰጠ ወክልና/ስልጣን ያካተተ ስለእያንዳንዱ አባል በተናጠል የሚያሳይ ወርሃዊ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የሜከላዊ ማከሚቻ ሥራዎችን ስለመጀመር</u>

1. ባለሥልጣኑ የምርት ገበያው ማሜልከቻ ሲያቀርብለት ሜከላዊ ማከሚቻው የኤሌክትሮኒክ መዛን ደረሰኞችን ለማውጣት፣ ለማስተላለፍ እንዲሁም ግብይቶችና እና መዛገቦች ሬከርዶች ላይ አሳሳች ድርጊት እንዳይፈጸም ለመከላከል በቂ ሥርዓቶችና የጥበቃ ዘደዎች ዘርግቷል ብሎ ካመነ ና ካረጋገጠ በዚህ ክፍል አንቀጽ 2 መሠረት የተመለከቱትን ማስፈርቶች ካሟላ፣ ሥራውን እንዲጀምር በጽሑፍ ይፈቅድለታል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ ክፍል አንቀጽ /1/ መሠረት የቀረበለትን ማሜልከቻ ሲመረምር የሜከላዊ ማከሚቻው ሥራውን ወጤታማ ሥርዓት ባለው መንገድ ያከናውን ዘንድ የሚያስፈልጉ አግባብ ያላቸውን ሁሉንም ጉዳዮች ከግምት ማስገባት አለበት፡፡ በተለይም የሚከተሉትን ሚረጋገጥ አለበት፡-
   1) የምርት ገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ የሜከላዊ ክምችቱን ደንቦች ሚጽደቁን፣
   2) በእያንዳንዱ አስቀማጭ ስም ሜከላዊ ማከሚቻው የባንክ ሂሣብ ለመክፈትና ለማያዝ ሥርዓት የዘረጋ ስለመሆኑ፣
   3) በአስቀሚጩ የባንክ ሂሣብ የሚደረጉ ለወጦች በክፍያ ሚፈጸሚ ተቋም እና የምርት ገበያው በሰየማቸው መዛኖች በሚሰጡ የኤሌክትሮኒክ ትዕዛዞች ወይም ሌሎች የትዕዛዝ መንገዶች የተደገፉ መሆናቸውን፣
   4) ሜከላዊ ማከሚቻው ወስጣዊ የሂሣብ ቁጥጥርና ሥርዓቶቹን ለማምገም፣ ለመከታተል እና ለመቆጣጠር በቂ ዘደዎች ያሉት ስለመሆኑ፣
   5) ሜከላዊ ማከሚቻው በየዕለቱ የእያንዳንዱን አስቀማጭ የየዕለቱን መዛገቦች የሚስታረቅ ዘዴ ያለው እንደሆነ፣
   6) የሜከላዊ ማከሚቻው አወቶማቲክ የሚጃ አያያዝና ማቅነባበሪያ ሥርዓቶቹ ህገወጥ በሆነ መንገድ ማንም ሊያገኛቸው፣ ሊለውጣቸው፣ ሊያጠፉቸው፣ ሊገልፃቸው ወይም መዛገቦችንና ሚጃዎችን ሊያባዛና ሊያሰራጫቸው በሚይችልበት ሜልኩ በቂ ጥበቃ ያላቸው ስለመሆኑ፣
   7) በሜከላዊ ማከሚቻው፣ በክፍያ ሚፈጸሚ ተቋሙ እና በምርት ገበያው በተሰየሙት መዛኖች መካከል የሚደረጉ የኤሌክትሮኒክ ግንኙነቶች ሚብ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ እንዳይገኝ ወይም እንዳይደረስ አስተማማኝ ስለመሆኑ፣
   8) ሜከላዊ ማከሚቻው በሜከላዊ ማከሚቻው፣ በክፍያ ሚፈጸሚ ተቋሙ፣ በምርት ገበያው በተሰየሙት መዛኖች መካከል ለሚደረጉ የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነቶች ደረጃቸውን የጠበቁ የአሰረጫጩና የኪድ አሰጣጥ ፎርማቶች ያዋቀረ ስለመሆኑ፣
   9) ሜከላዊ ማከሚቻው መዛገቦቹ ከመጥፋት ወይም ከመወደም ይጠበቁ ዘንድ በቂ ሥርዓቶችንና ዘደዎችን ሚስቀመጡና ሜከላዊ ማከሚቻው ከሚገኝበት ሌላ ቦታ የሪከርድ ማጠበበቂያ ዘደዎች ተዘጋጅተው እንደሆነ፣
   10) ሚጃ ለማጠበበቂያነት የሚቀመጥባቸውን ቦታዎች ጨምሮ በአካል ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ወደ ቢሮዎች፣ ቅጥር ግቢዎች፣ መገልገያዎች፣ መሣሪያዎች፣ አወቶማቲክ የሚጃ ማቅነባበሪያ ሥርዓቶች፣ የሚጃ ማስቀመጫ ቦታዎች እና ሜከላዊ ማከሚቻውን፣ የክፍያ ሚፈጸሚ ተቋሙን፣ በምርት ገበያው የተሰየሙ መዛኖችን የሚያገናኙ

2/ ባለስልጣኑ እንደነገሩ ሁኔታ ለሚከላዊ ማከማቻው፣ ለክፍያ ሚጸሚ ተቋሙ እና ለተሰየሙት የክፍያ ማዛዣዎች ምርመራውን ወይም ማጣራቱን ከማዛዙ ወይም ከሚድረጉ በፊት ከአስር ቀናት የማያንስ ማስታወቂያ ይሰጣቸዋል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው ቢኖርም፡ ባለሥልጣኑ ለአስቀማጮች ጥቅም ሲባል የተጠቀሰውን ማስታወቂያ ማስጠት አያስፈልግም ብሎ ሲያምን በጽሑፍ በሚሰጠው ትዕዛዝ ምርመራው ያለማስታወቂያ እንዲካሄድ ሊያዝ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## የምርት ገበያው የግልግል ዳኝነት

1. የምርት ገበያው እንደ አግባብነቱ አባላትንና ደንበኞችን የሚመለከቱ የግልግል ደንቦችን ማውጣትና ማስፈፀም፣ እንደዚሁም የግልግል ዳኝነት ሚቋቋምና ለግልግል ዳኝነት የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችን ማቅረብ አለበት፡፡
2. የምርት ገበያው ፍትሐዊና ተመጣጣኝ የግልግል ዳኝነት አገልግሎቶችን በቀጥታ ወይም በሌላ ድርጅት አማካኝነት ለአባላት ዝግጁ ሚድረግ አለበት፡፡
3. የምርት ገበያ የግልግል ዳኝነት አገልግሎት፡ -
   1/ አቤቱታ በገለልተኛና ሀቀኛ ወሳኔ ሰጭ እንዲወሰን ለተከራካሪ ወገን ዕድል የሚሰጥ፣
   2/ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን በራሱ ወጪ በጠበቃ እንዲወከል መብት የሚሰጥ፣
   3/ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን የቀረበበት አቤቱታ/ክስ በበቂ ሁኔታ እንዲደርሰው፣ በሁሉም ክሶች ላይ የማሰማት እና የመከላከል ዕድል የሚሰጥ እና የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ እንዲቀርብ የሚፈቅድ እንደዚሁም ለፈጣን ወሳኔ አጋጣሚን የሚያመቻች፣
   4/ በምርት ገበያው ወስጥ ይግባኝ የሚይባልበት ፈጣንና የመጨረሻ በፅሑፍ የሚሰጥ ወሳኔን ተፈፃሚነት የሚፈቅድ፣ እና
   5/ የተከራካሪ ወገኖች ክፍያዎችንና ወጪ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. ደንበኞች የግልግል ዳኝነት አገልግሎቱን የሚጠቀሙት በፍቃደኝነት ይሆናል፡፡
5. ደንበኛን የሚይመለከትና አባል ከአባል የሚያደርገውን ክርክር ለመፍታት የሚያገለግለው የምርት ገበያው የግልግል ዳኝነት ሥራ ከደንበኞች ቅሬታ ወይም አቤቱታ አፈታት ተለይቶ ራሱን ችሎ የሚካሄድ መሆን አለበት፣
6. የምርት ገበያው ገለልተኛ የሆኑ የግልግል ዳኞች ዝርዝርን ሚያዝ ይኖርበታል፣
7. በምርት ገበያው የግልግል ዳኝነት ሥራ ላይ ለማገልገል የሚበቁ የግልግል ዳኞች በምርት ገበያው የሚሰጥ ወይም የተጠየቀን ሥልጠና ማጠናቀቅ እና፡ -
   1/ በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ እና በግልግል ዳኝነት የ5 (አምስት) ዓመት አገልግሎት፣ ወይም
   2/ ለምርት ገበያው ንግድ አግባብነት ባለው ማስክ የማስተርስ ዲግሪ እና በግልግል ዳኝነት የ5 (አምስት) ዓመት ልምድ ወይም ተመጣጣኙን ሊኖራቸው ይገባል፡፡
8. የምርት ገበያው የደንበኛን የክርክር መፍቻ ዘዴዎችን ለማመቻቸት ላለበት ኃላፊነት በባለሥልጣኑ ዕወቅና ለተሰጣቸው የብሔራዊ የምርት ገበያ ግብይት ፈፃሚዎች ማህበርን ወይም ሌላ ድርጅትን ሊወክል ይችላል፤ ሆኖም የምርት ገበያው ይህን ኃላፊነቱን በወከልና ከሰጠ በብሔራዊ የምርት ገበያ ፈፃሚዎች ማህበር ወይም ሌላ ማሰል ድርጅቶች በአጥፊው አባል ላይ የሚሰጠው ወሳኔ በተገቢው ሁኔታ እንዲፈፀም ትዕዛዝ ማስጠትን ጨምሮ ማንኛወም ወሳኔ የራሱ የምርት ገበያው ወሳኔ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የምርት ግብይት ፈፃሚዎችን ዕወቅና ስለማስጠት

1. በባለሥልጣኑ የምርት ግብይት ፈፃሚ ት ዕወቅና ካልተሰጠ በስተቀር በምርት ገበያ ደንብ መሠረት የምርት ገበያ ወሎችን መግዛት ወይም መሸጥ፣ የግዥ ወይም የሽያጭ ጥያቄ ማቅረብ፣ የግብይት ትዕዛዞችን መቀበል የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውም በምርት ግብይት ፈፃሚ ት ዕወቅና ለማግኘት የሚፈልግ ሰው የሚፈልገውን የዕወቅና ዓይነት እና በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ በአንቀጽ 17 የተቀመጡትን መሥፈርቶች የሚያከብርና ወደፊትም ማክበሩን የሚቀጥል መሆኑን ገልጾ በቅጽ 1 ወይም 2 መሠረት ለባለስልጣኑ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡
3. **ዕወቅና ስለሚጣቸው የምርት ገበያ ተሳታፊዎች ዓይነት**
   1. አባል፡- ለእያንዳንዱ የአባል ዓይነት የተሰጠው ትርጉም በገበያው የወስጥ ደንብ የተገለፀው ሆኖ ተገበያይ አባል፣ አገናኝ አባል፣ ወስን ተገበያይ አባል፣ ወስን አገናኝ አባል፣ ወይም በገበያው ደንብ የሚገለፅ ሌላ ዓይነት አባል፣
   2. ተባባሪ አባል፣
   3. በአባሉ ሥልጣን የተሰጠው ተወካይ፡፡

**4. የአባል ዕወቅና**

1. ማንኛውም ሰው እንደ አባል ዕወቅና ካላገኘ በቀር፡-

   /ሀ/ በምርት ገበያው የንግድ ወሎች በራሱ ወይም በሌሎች ሐሳብ ማገድ፣ ወይም

   /ለ/ ራሱን የምርት ገበያ ንግድ እንደሚያከናወን ሰው አስመስሎ ማቅረብ አይችልም፡፡

2. ማንኛውም ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ አካል /ድርጅት/ እያንዳንዱ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ በዳይሬክተርነቱ ወይም በሠራተኛነቱ በምርት ገበያው የንግድ ወሎች /ግብዓቶች/ ለሚከናወን ንግድ ዓላማ ለድርጅቱ እንዲሠራ ወይም በድርጅቱ ስም እንዲንቀሳቀስ በድርጅቱ ተገቢው ወክልና ካልተሰጠው በቀር የምርት ገበያወን ንግድ ሊያከናወን አይችልም፡፡

**5. ስለአባል ተወካይነት ዕወቅና**

1. ማንኛውም የአባል ተወካይ በባለስልጣኑ የአባል ተወካይነት እወቅና ካልተሰጠው በቀር በአባሉ ስም በምርት ገበያው ወስጥ ሊነግድ አይችልም፡፡
2. ማንኛውም ሰው፡-

   /ሀ/ እንደ የአንድ አባል ሠራተኛ ወይም ወኪል በአባሉ ስም ወይም ስለ አባሉ ወይም ስለ አባሉ ጥቅም የተንቀሳቀሰ ከሆነ፣

   /ለ/ ከአባሉ የምርት ገበያ ንግድ ጋር በተያያዘ የተንቀሳቀሰ ከሆነ፣

   /ሐ/ የአባል ልዩ ተወካይ ሆኖ ከሰራ፣

   /መ/ አንድ ሐሳብ ባለሟ ወይም ፀሐፊ ወይም ገንዘብ ያዥ በመደበኛነት ከሚሠራው ሥራ ወጪ ለአባሉ የሚሰራ ከሆነ፣ ሥልጣን እንዳለው ወኪል እንደተንቀሳቀሰ ይቆጠራል፡፡

3. ከዚህ በላይ የተገለፀው አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደለት በቀር ማንኛውም አባል ከ4 የመድረክ ተወካዮች በላይ ሊኖሩት አይችልም፡፡
4. የምርት ገበያው በልዩ ሁኔታ ካልፈቀደለት በስተቀር ማንኛውም አባል በአንድ የግብይት ክፍለ ጊዜ (Trading Session) በግብይት መድረኩ ወስጥ ከ2 በላይ ተወካዮችን ሊያሠማሩ አይችልም፡፡

6. **ለአባላት ዕውቅና ለመስጠት የሚያስፈልግ መሥፈርት**

**1. የምርት ገበያው ይሁንታ**

በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ዕውቅና እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው የምርት ገበያው አባል ለመሆን ያቀረበው ማመልከቻ በምርት ገበያው ይሁንታ ስለማግኘቱ /መፅደቁ/ ማስረጃ ካልቀረበ የአባል ዕውቅና አያገኝም /እንደ አባል አይታወቅም/፡፡ የምርት ገበያው ይሁንታ በአባሉ ሥልጣን የተሰጠው ወኪል ይሁንታን ይጠቀልላል፡፡

**2. የአባላት ፋይናንስ መመዘኛዎች**

ማንኛውም ሰው የምርት ገበያውን የፋይናንስ መመዘኛዎች እንደሚያሟላ ባለስልጣኑን በሚያሳምን ሁኔታ ካላረጋገጠ /ካላሳየ/ በቀር እንደ አባል ዕውቅና አያገኝም/አይታወቅም/፡፡ በአባል ለመታወቅ /የአባልነት ዕውቅና/ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ሁሌም የዚህን ክፍል መመዘኛዎች /ድንጋጌዎች/ ማክበር ያለበት ሲሆን መመዘኛዎቹን ማሟላቱን /ድንጋጌዎቹን ማክበሩን/ ባለሥልጣኑን በሚያሳምን ሁኔታ ማረጋገጥ አለበት፡፡

/ሀ/ ማንኛውም አባል ተገበያይ አባል ከሆነ የተጣራ ሀብት ብር 500,000 (አምስስ መቶ ሺህ)፣ አገናኝ አባል ከሆነ ብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን)፣ ያለው መሆኑን ማረጋገጥና በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ 17 የተገለፀውን ማሟላት አለበት፡፡

/ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተመለከተውን ያላሟላ ወይም መመዘኛዎቹን ስለማሟላቱ ማረጋገጥ ያልቻለ አባል በምርት ገበያው ደንብ መሠረት የደንበኛን ሂሳብ ማዛወር፣ እንደዚሁም መመዘኛዎቹን ማሟላቱን እስከሚያስረዳ ድረስ እንደ አባል የንግድ እንቅስቃሴ ማድረግን ወዲያውኑ ማቆም እና ይህንኑ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ በመፍረስ ላይ ያለ ድርጅት ቀሪ ሥራን ለማጠናቀቅ ሲባል በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንዲሰራ በባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደለት በስተቀር በምርት ገበያው የንግድ ሥራ ማከራት አይችልም፡፡ በተጨማሪ አባሉ መመዘኛዎቹን ሊያሟላ የሚያስችለው ችሎታ እንዳለው ባለስልጣኑን በሚያሳምን ሁኔታ ያረጋገጠ ከሆነ በባለስልጣኑ አባሉ የደንበኛን ሂሳብ ሳያዛወር እንዲሁም ከላይ በተቀመጠው መሠረት የንግድ ሥራውን መሥራት ሳያቆም ለ30 የሥራ ቀናት እንዲቆይ ማድረግ ይችላል፡፡ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን መመዘኛዎች ባላሟላ አባል ላይ ሊወስድ የሚችለውን እርምጃ እንደሚከለክል ተደርጎ ሊተረጎም አይችልም፡፡

**3. የብቃት ማረጋገጫ መመዘኛዎች**

በአባልነት ዕውቅና ማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሀላፊና ዳይሬክተር በምርት ገበያው የሚዘጋጀውን አግባብነት ያለው የአባላት የብቃት ማረጋገጫ ፈተናን ማለፍ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪ በምርት ገበያው የሚሰጥ ማንኛውንም ሥልጠና ወይም ለተወሰነ ጊዜ በተከታታይ የሚሰጥ ትምህርትን መከታተል ያለበት ሲሆን በአዋጁ፣ በዚህ መመሪያ ወይም በምርት ገበያው የውስጥ ደንቦች መሠረት ለባለሥልጣኑ፣ ለምርት ገበያው ወይም ለሕዝቡ ያለበትን ኃላፊነት ሚዛኑን /ማንዘቡን/ ለማረጋገጥ የተዘጋጀ የምርት ገበያውን ተከታታይ የብቃት መመዘኛ ፈተናዎችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

**4. የኋላ ታሪክ ማረጋገጫ መሥፈርት**

የአባልነት ዕውቅና የሚፈልግ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ ከሆነ የዚሁ አካል ሀላፊዎችና ዳይሬክተሮች በኢኮኖሚ እና የገንዘብ ጥቅሞች ወንጀሎች ወይም የመታመንነትን በሚቃንሱ ማጭበርበር ወንጀሎች ጥፋተኛ አለመሆናቸውን በበቂ ሁኔታ ለባለስልጣኑ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

**5. ብሔራዊ የግብይት ፈፃሚዎች ማህበር አባልነት**

የአባልነት ዕውቅና የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ አዋጅ መሠረት በሚቋቋመው ብሔራዊ የግብይት ፈፃሚዎች ማህበር አባል መሆን ይኖርበታል፡፡

**6. የንግድ ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ**

/ሀ/ ማንኛውም አባል ዕውቅና ለማግኘት የተሰማራበትን የንግድ ሥራ በተመለከተ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ አለበት፡፡ ዕውቅና ጠያቂው ያቀረበው የንግድ ፈቃድ በሌላ ሕግ የብቃት ማረጋገጫ የሚጠየቅበት ምርትን የሚመለከት ከሆነ ይህንኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

/ለ/ ማንኛውም ዕውቅና ያለው አባል አግባብ ያለው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር የብቃት ማረጋገጫ የሚጠየቅበትን ምርት ለራሱ ማበያየት አይችልም፡

/ሐ/ ከዚህ በላይ ያለው ድንጋጌ ማንኛውም ዕውቅና ያለው አገናኝ ወይም ወሰን አገናኝ አባል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በተሰጠው ደንበኛው ስም የብቃት ማረጋገጫ የሚጠየቅበትን ምርት ከማካሄድ አያግደውም፡፡

**7. የአባል ተወካይ ዕውቅና ስለሚያገኝበት ሁኔታ**

**1. የምርት ገበያው ይሁንታ**

በባለሥልጣኑ የሚሰጠው ዕውቅና እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው የአባል ተወካይነት ዕውቅና ለማግኘት ያቀረበው ማመልከቻ በምርት ገበያው ይሁንታ ስለማግኘቱ /ስለ መፅደቁ/ ማስረጃ ካላቀረበ በቀር ሥልጣን እንዳለው የአባል ተወካይ ዕውቅና አያገኝም፡፡

የምርት ገበያው ይሁንታ ለወካዩ ሰው የሚደረግ የአባልነት ይሁንታን ይጨምራል፡፡

**2. የብቃት ማረጋገጫ መመዘኛ**

በአባል ተወካይነት ዕውቅና ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በምርት ገበያው የሚዘጋጅ እና ችሎታውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ማለፍ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ይኸው የአባል ተወካይ በምርት ገበያው የሚሰጥ ማንኛውንም ስልጠና እንደዚሁም ለተወሰነ ጊዜ በተከታታይ የሚሰጥ ትምህርትን መከታተል ያለበት ሲሆን በአዋጁ፣ በዚህ መመሪያ ወይም በምርት ገበያው የውስጥ ደንብ መሠረት ለባለሥልጣኑ፣ ለምርት ገበያው ወይም ለሕዝብ ያለበትን ኃላፊነት /ግዴታ/ ማንዘቡን ለማረጋገጥ የተነደፈ የምርት ገበያውን ተከታታይ የብቃት መመዘኛ ፈተናዎችን ማለፍ ይኖርበታል፡፡

**3. የኋላ ታሪክ ማረጋገጫ መሥፈርት**

በአባል ተወካይነት የወክልና ዕውቅና እንዲሰጠው የሚፈልግ ሰው በኢኮኖሚ እና የገንዘብ ነክ ወይም የዕውቅና ጠያቂውን ግለሰብ ስብዕና በሚቀንሱ ወንጀሎች ጥፋተኛ አለመሆኑን ለባለሥልጣኑ በአጥጋቢ ሁኔታ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**8. በግብይት ፈጻሚት ዕውቅና ለማግኘት ማመልከቻ የሚቀርብበት ሥነ ሥርዓት**

1. በምርት ግብይት ፈጻሚት ዕውቅና ማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የዕውቅና ማጠየቂያ ማመልከቻውን አግባብነት ካላቸው አባሪዎችና ከምርት ገበያው ቅድመ ይሁንታ ደብዳቤዎች ጋር በማያያዝ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. **ማመልከቻው የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፣**

/ሀ/ እንደጉዳዩ አግባብነት የተሞላ ቅፅ 1 ወይም 2፣

/ለ/ የተሟላ የምርት ገበያ የአባልነት ማመልከቻ አባሪዎችን እንደያዘ እንደዚሁም አግባብነት ካላቸው አባሪዎችና ከምርት ገበያ ቅድመ ይሁንታ ደብዳቤዎች ጋር፣

/ሐ/ አመልካቹ በአዋጁ ክፍል ሶስት እንደዚሁም በዚህ ደንብ ድንጋጌ መሠረት እንደሚሰራ የተሰጠ ማረጋገጫ

/መ/ አመልካቹ በኢኮኖሚ በገንዘብ ነክ ወይም የሙያ ታማኝነቱን ዝቅ በሚያደርጉ ወንጀሎች ጥፋተኛ አለመሆኑን የሚያሳይ ማረጋገጫ

/ሠ/ አመልካቹ በበቂ ዝርዝር የለያቸው በሚስጥር የሚጠበቁ ተደርገው የሚቆጠሩ በማመልከቻው ላይ ያሉ መረጃዎች ሲኖሩ መረጃዎች በሚስጥር እንዲያዙ በማስረጃ ተደግፎ የቀረበ ጥያቄ፡፡

**9. ማመልከቻው ስለሚወሰንበት ጊዜ**

1. በዚህ አንቀፅ ኑዑስ አንቀፅ 2 በተደነገገው ሁኔታ ካልሆነ በቀር ባለስልጣኑ የምርት ገበያ ፈፃሚ ዕወቅና ለማግኘት የቀረበወን ማመልከቻ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር 7/ሰባት/ የሥራ ቀናት ወስጥ ይወሰንዋል፡፡ ባለሥልጣኑ አግባብ ሆኖ ካገኘው ማመልከቻወን ሊያፀድቀው ወይም ወድቅ ሊያደርገው ወይም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ የምርት ገበያ ተሳታፊወን ዕወቅና ሊሰጥ ይችላል፡፡ ባለሥልጣኑ በማመልከቻው ላይ የሚታየወን ጉድለት ለይቶ በማውጣት ማመልከቻው ያልተሟላ መሆኑን ለአመልካቹ ያሳወቀው እንደሆነ ጉዳዩ የሚወሰንበት ዕለት ማመልከቻው ተሟልቶ እስከሚቀርብበት ቀን ድረስ ይቆያል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ጊዜያዊ የምርት ግብይት ፈፃሚነት ዕወቅና በአፋጣኝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀፅ መሠረት የሚሰጥ ዕወቅና ባለሥልጣኑ ባስቀመጠው ቅድመ ሁኔታና የጊዜ ገደብ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
3. የምርት ግብይት ፈፃሚው የዕወቅና ቅድመ ሁኔታዎቹ በተሟሉ ጊዜ የጊዜያዊ ዕወቅና የማብቂያ ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ቋሚ ዕወቅና እንዲያገኝ ማመልከት አለበት፡፡

**10. የዕወቅና ማመልከቻን ስለአለመቀበል**

1. ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሲከሰቱ ለምርት ግብይት ፈፃሚነት ዕወቅና የቀረበወን ማመልከቻ ላይቀበለው ይችላል፡፡

/ሀ/ ማመልከቻው በአዋጁ ክፍል 3 እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 እና 7 መሠረት ያልተዘጋጀ ሲሆን፣

/ለ/ አመልካቹ የአዋጁንና የዚህ ደንብ መመዘኛዎችን ሳያሟላ ሲቀር፣

/ሐ/ አመልካቹ ንግዱን ለማካሄድ አላማ ሲል ከእርሱ ወይም ከቀጠረው ወይም ከተባበረው ሰው ጋር የተያያዘ ወይም በንግዱ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉ ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ በባለስልጣኑ የተጠየቁ መረጃዎችን ለማስጠት ሳይችል ሲቀር፣

/መ/ አመልካቹ የከሰረ ሲሆን ወይም ድርጅትም በሆነ ጊዜ ከስሮ በመፍረስ ላይ ያለ ሲሆን፣

/ሠ/ ባለስልጣኑ አመልካቹ፣ የአመልካቹ ዳይሬክተሮች፣ ኃላፊዎች ወይም ወኪሎች ብቃት ከምርት ግብይት ፈጻሚነት የሥራ ባህርይ አንፃር ሲታይ በቂ ስለመሆኑ አሳማኝ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር፣

/ረ/ አሜልካቹ ወይም ዳይሬክተሮቹ ወይም ሀላፊዎቹ ወይም ወኪሎቹ ወይም ሠራተኞቹ በኢኮኖሚ እና የገንዘብ ነክ ወይም ሞያዊ ብቃትን በሚያሳንስ ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ ወይም አሜልካቹ ሜልካም ሥነ ምግባር የሌለው ስለመሆኑ ሲታመንበት፣

/ሰ/ አሜልካቹ በምርት ገበያው የተቀመጠ/የተወሰነን የፋይናንስ መመዘኛ ሳያሟላ ሲቀር፣

/ሸ/ የአሜልካቹ ዕወቅና ማስጠት ለሕዝብ ጥቅም ተፃራሪ ሲሆን፣

2. ማንኛወም ዕወቅና ለማግኘት ያመለከተ ሰው በግብይት ፈጻሚነት ዕወቅና በሚከለከልበት ጊዜ ዕወቅና በተከለከለበት ውሳኔ ላይ ለባለሥልጣኑ አቤቱታ አቅርቦ የማስማትና፣ በባለሥልጣኑ የሚሰጠዉን ውሳኔ የሚቃወመው ሆኖ ሲገኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡

## 11. ዕወቅና ስለማሳደስ

1. ዕወቅናው እንዲታደስለት የሚፈልግ ማንኛወም ግብይት ፈፃሚ በየሶስት ዓመቱ ፀንቶ የሚገኘው የዕወቅና ጊዜ ከተጠናቀቀበት ቀን ቀጥሎ ባሉት አራት ወራት ወስጥ አስፈላጊዉን መመዘኛ በማሟላት እና የተዘጋጀዉን ቅጽ በመሙላት የእወቅና እደሳት ማመልከቻ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተወሰነው ጊዜ ወስጥ የዕወቅና እደሳት ማመልከቻ ያላቀረበ ግብይት ፈፃሚ በባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደለት በስተቀር በምርት ገበያው የሚያደርገዉን የግብይት ስራ ወዲያዉኑ በማቆም ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር እና ከአንድ ወር ላነሰ ጊዜ ብር 2,000 /ሁለት ሺህ/ ቅጣት በመክፈልና አስፈላጊዉን መመዘኛ በማሟላት በቀጣዮቹ ሁለት ወራት ወስጥ የዕደሳት ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተወሰነው ጊዜ ካለፈ በኋላ የዕወቅና ዕድሳት ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛወም ግብይት ፈፃሚ የዘገየው ከቁጥጥሩ ውጭ በሆኑ ምክንያቶች መሆኑን አስረድቶ በባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ማመልከቻው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
4. አሜልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 መሠረት ዕወቅናው ካልታደሰ ወይም ዕወቅናዉን ለማሳደስ ካልፈለገ በምርት ገበያው ያለዉን የአባልነት መቀመጫ ለሌላ ሰው የማስተላለፍ መብት ይኖረዋል፡፡ የአባልነት መቀመጫ የሚተላለፍበት ዝርዝር ሥነ ሥርዓት አግባብነት ያላቸዉን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንቦች የተከተለ ይሆናል፡፡

## 12. ዕወቅና ስለሚታገድበት ወይም ስለሚሰረዝበት ሁኔታ

ባለሥልጣኑ የሚከተለው ሲከሰት የምርት ግብይት ፈፃሚ ዕወቅና 180 /መቶ ሰማንያ/ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ለማገድ ወይም እወቅናዉን ለማንሳት ይችላል፡፡

1. የምርት ግብይት ፈፃሚው የዕወቅና ቅድመ ሁኔታዎችን ካልፈጸመ ወይም እየፈፀመ ካልሆነ፣
2. የምርት ግብይት ፈፃሚው፣ ዳይሬክተሮቹ፣ ሀላፊው፣ ወኪሉ ወይም ሠራተኛው አዋጁንና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች እንዲሁም የባለስልጣኑን ትዕዛዞች የጣሰ ወይም በመጣስ ላይ ከሆነ፡፡

## 13. የመስማት ዕድልና የይግባኝ መብት

1. በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 19 መሠረት ዕወቅናው በሚታገዱበት ወይም በሚሰረዝበት ጊዜ ለዕወቅና ያመለከተ ማንኛወም ሰው ወይም ዕወቅናው የታገደበት ወይም የተሠረዘበት የምርት ግብይት ፈፃሚ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታዉን የማስማት ዕድል አለው፡፡ የቅሬታ ማስማት ሂደቱ በባለስልጣኑ ተመዝግቦ ይቀመጣል፡፡

2. የዕወቅና ጥያቄው ወድቅ በሆነ ወይም ዕወቅናው በታገደ ወይም ቀሪ በሆነ በ30 /ሰላሳ/ ቀናት ወስጥ የምርት ግብይት ፈፃሚው ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ካላቀረበ በቀር ጥያቄዉን ወድቅ ያደረገው ወይም ዕወቅናወን ያገደው ወይም የሰረዘው ወሳኔ የሜጨሻ ይሆናል፡፡

3. በባለሥልጣኑ ፊት የተሰጠ ምስክርነት ወይም የተወሰደ ወይም የቀረበ እና በአግባቡ የመዝገብ አካል የተደረገ ማስረጃ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የቀረበ ማስረጃ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

**14. ማመልከቻን ማንሳት**

ዕወቅና ለማግኘት የቀረበ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ የቀረበወን ጥያቄ እንዲነሳ ማመልከቻ በማቅረብ ሊነሳ ይችላል፡፡ ለዕወቅና የቀረበን ማመልከቻ /ጥያቄ/ ማንሳት ማመልከቻው በባለሥልጣኑ እየተመረመረ እያለ የተከሰቱ ድርጊቶችን ወይም ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ በባለሥልጣኑ የተወሰደ ወይም የሚወሰድ እርምጃን አይለወጠውም፡፡

**15. ዕወቅናው እንዲሰረዝ ስለመጠየቅ**

ዕወቅና ያገኘው የምርት ግብይት ፈፃሚ ለባለሥልጣኑ ጥያቄ በማቅረብ በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት ዕወቅናው እንዲሰረዝ ማድረግ ይቻላል፡፡ የዕወቅናው መሰረዝ ዕወቅናው በባለሥልጣኑ እየተመረመረ እያለ የሚከሰቱ ድርጊቶችን፣ እንቅስቃሴዎች ወይም ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ በባለሥልጣኑ የተወሰደ ወይም ሊወሰድ የሚችል እርምጃን አይለውጥም፡

**16. የግብይት ፈፃሚዎችን ዝርዝር በህትመት ስለማውጣት**

በባለሥልጣኑ ዕወቅና ያገኙ፣ ዕወቅናቸው የተሻረ፣ የታገደ የምርት ግብይት ፈፃሚዎችን ዝርዝር በመዝገብ በማስገባት በየወሩ በብሔራዊ የምርት ግብይት ፈፃሚዎች ማህበር ወይም በታወቁ ዜና ማሰራጫ ሕትመቶች ወይም ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነበት የማሠራጫ ዘዴ እንዲታተም ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ስለግብይት ፈፃሚዎች ንግድ አሰራር</u>

**1. እያንዳንዱ የምርት ገበያ ተሳታፊ የሚከተሉትን አጠቃላይ የሙያ የሥነ-ምግባርና ግብረ-ገብ መስፈርቶችን መከተል አለበት፡፡**

1. ሙያዊ ስነምግባርን ማክበር

እያንዳንዱ አባል ንግዱን የላቀ ሙያዊ ባህሪን በሚያሳይ አኳኋን ማከናወን ያለበት ሲሆን ሙያውን፣ ኢንዱስትሪወንና የምርት ገበያወን ማክበር ይኖርበታል፡፡ አባሉ ዕወነትን መናገር እንደዚሁም ተቀባይነት ያላቸው የታማኝነት እና የቅንነት መርኾዎችን በመከተል ሥራውን ማከናወን አለበት፡፡

2. የደንበኞች ኃላፊነት

ማንኛወም አገናኝ አባል፣

/ሀ/ በደንበኛው ስም ግብይት ከሚፈፀሙ አስቀድሞ በገበያው ደንብ የተገለፀውን መሠረታዊ ሀሳብ የያዘ ወል ከደንበኛው ጋር ማድረግ አለበት፡፡

/ለ/ የደንበኛወን ሕጋዊ ዓላማ በትጋትና በታማኝነት ሜፈፀም ይኖርበታል፡፡ ሥራን ለደንበኛው ሲያከናወንም የራሱን ጥቅምና ፍላጎት ከደንበኛው ጥቅም ማስበለጥ አይገባወም፡

/ሐ/ የደንበኛው የሽያጭ ገንዘብ በገበያው ደንብ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ወስጥ ለደንበኛው መድረሱን የሚረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

/መ/ ደንበኛው ግዥ እንዲፈፀምለት ወደባንክ ያስገባው ገንዘብ በደንበኛው ትዕዛዝ መሠረት ግዥ ለሚፈፀም ብቻ የዋለ ማሆኑን፣ እንዲሁም ከግብይት የተረፈ ገንዘብ ለደንበኛው በወቅቱ መመለሱን የሚረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

/ሠ/ ለእያንዳንዱ ደንበኛ ያከናወነወን የግብይት እንቅስቃሴ የሚያሳይ የሂሳብ ሪፖርት በየወሩ በጽሑፍ ለደንበኛው ማስጠት አለበት፡፡

/ረ/ የምርት ገበያወን ንግድ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሁልጊዜ ወይም ሁለቱ ወገኖች በተስማሙበት ጊዜ በምርት ገበያው የንግድ አሠራር ላይ ለደንበኛው ምክር ማስጠት አለበት፡፡

3. የጥቅም ግጭት

ማንኛወም አገናኝ አባል በደንበኛወና በርሱ መካከል ያለን የሚታወቅ የጥቅም ግጭት ለደንበኛው መግለጽ አለበት፡፡ እያንዳንዱ አገናኝ አባል ግጭቱን ለመፍታት /በቂ/ ሚዛናዊ መንገዶችን ማጠቀም አለበት፡፡

ማንኛወም አገናኝ አባል የጥቅም ግጭቱ ሳይገለጽ እንዲቆይ ተገቢነት የሌለው አካሄድን ሊከተል አይገባም፡፡

4. ሚስጥራዊነት

ማንኛወም አባል በእምነት የተሰጠወን ሕጋዊ የንግድ ሚስጀ በሚስጀ ሰጪው ሚስጀወን ይፋ እንዲያደርግ ካልተፈቀደለት ወይም በሕግ የተወሰነ የሚስጥር ማቆያ ጊዜ ካላበቃ በሚስጥር ማያዝ አለበት፡፡

5. ፍትሀዊ ንግድ

ማንኛወም አገናኝ አባል ከደንበኛው ጋር የሚኖረው ግንኙነት ፍትሀዊ እንዲሆን ተገቢወን ጥረት ሚድረግ ይኖርበታል፡፡ ማንኛወም አባል በማጭበርበር፣ በሚታለል፣ በሚደበቅ፣ በሥራ አጋጣሚ እጁ ወስጥ የገባን ሚስጀ ያልሆነወን ነው ብሎ በማቅረብ አላግባብ በማጠቀም፣ ፍሬ ነገርን በማዛባት ወይም ማናቸወንም የሚጥገባ የንግድ ተግባር በሚፈፀም አላግባብ ሊጠቀም አይገባም፡፡

6. ተከታታይ ትምህርት

ማንኛወም አባል የቅርብ ጊዜ የንግድ ለወጦችን ለመከታተል የሚያበቁ እርምጃዎችን በመውሰድና በምርት ገበያው የሚሰጡ ሥልጠናዎችን በመከታተል በምርት ገበያው ንግድ ላይ ዕወቀት እንዲኖረው ጥረት ሚድረግ አለበት፡፡

7. ሕግን ማከበር

እያንዳንዱ አባል እንደአግባብነቱ የንብረት አስተዳደርን፣ የንብረት ባለቤትነትን ማዘረታታትን የሚመለከቱ ሕጎችንና የፌደራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር ህግጋትና ደንቦችን፣ እንዲሁም ከንብረት አስተዳደር ጋር የተያያዙ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን ማክበር አለበት፡፡

2. **ማንኛውም የምርት ግብይት ፈፃሚ ሠራተኞቹን ወይም ወኪሎቹን ወይም ስለእርሱ ሆነው የራሳቸውን የምርት ገበያ እንቅስቃሴ በሚያደርጉ ሠራተኞች እና ወኪሎች ላይ ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡**

3. **ማንኛውም የግብይት ፈፃሚ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ብቻ ሳይወሰን የንግድ ሥራውን በተገቢው ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችሉትን የሂሳብ ማዛግብት ሰነዶች እንዲሁም፡ -**

   1. የደንበኛውን ስም፣ አድራሻውን፣ ሥራውን፣ እና የደንበኛ ሒሳብ ተቆጣጣሪን፣

   2. በተለየ ሒሳብ ወስጥ ያለ በየቀኑ የሚሰላ የደንበኛ ተቀማጭ ገንዘብ ድምር እና የምርት ገበያው ተሳታፊ በዚህ የደንበኛ ሒሳብ ላይ ያለው ቀሪ ጥቅም፣

   3. ተቀማጭ የሆነ፣ ወጪ የተደረገ፣ የተላለፈ የደንበኛ ሂሳብ እና በዝግ ግብይት ከኪሣራ ወጪ ወይም ገቢ እንደዚሁም ለምርት ገበያ ፈፃሚ የተከፈለ የኮሚሽን ክፍያን ጨምሮ ወደ እያንዳንዱ ደንበኛ ሒሳብ የገባ ገቢን ወይም የወጣ ወጪን በተናጠል የሚያሳይ የሒሳብ ሌጀር ማዛገብን፣

   4. የምርት ገበያው ወሎችን ከሚመለከት ንግድ ጋር የተያያዙ ግብይቶች የተሟሉ፣ በስርዓት የተደራጀ ማዛገቦችና አግባብነት ያላቸው ዳታዎችና ማስታወሻዎች በማዛግብቶቹ በምርት ገበያ ወል የሚመለከቱ የንግድ ሂደቶች ላይ የሚዘጋጁ ትዕዛዞችን (የተሞሉ፣ ያልተሞሉ፣ የተሰረዙ)፣ የንግድ ካርዶችን፣ የፊርማ ካርዶችን፣ መፅሐፎችን፣ ሌጀሮችን፣ የተሰረዙ ቼኮችን፣ የሚያጋገጨ ሰነድ ግልባጮችን፣ የግዥና ሽያጭ መግለጫ ግልባጭ፣ እና ማዛገቦችን የሚያካትት ሲሆን፣ ከነዚሁ በተጨማሪ

   5. አነስተኛ የፋይናንስ መጠዛኛ በሚጠይቅበት ጊዜ የምርት ገበያው በተወሰነው ጊዜ ወስጥ በምርት ገበያው እና በባለስልጣኑ ዘንድ የሚቋመጥ በሂሳብ ማዛገብ አያያዝ አሰራር መሠረት የፋይናንስ ሪፖርት ማዘጋጀት፣

   6. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚያዙ የሂሣብ ማዛግብትና ሰነዶች በማዛገብነት ተቀማጭ ከሆነበት ቀን ጀምሮ እስከ አምስት አመት ድረስ ሊገኙ በሚችሉበት ሁኔታ (ተደራጅተው) መያዝ አለባቸው፡፡ እነዚህ የሂሳብ ማዛግብትና ሰነዶች የባለስልጣኑ ወኪል ለሚያደርገው ምርመራ ክፍት መሆን አለባቸው፡፡

**4. ሪፖርቶች**

ማንኛውም የምርት ግብይት ፈፃሚ በዚህ ክፍል በአንቀጽ 3 ማሥፈርቶች መሠረት ከተያዙ ማዛገቦች በመነሳት ባለስልጣኑ በመመሪያ ወይም በትዕዛዝ በሚወሰነው ጊዜ፣ ቦታና አይነት መሠረት ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

5. **በአዋጁ የአንቀፅ 27 ድንጋጌዎች ከተከለከሉት በተጨማሪ ማንኛውም የግብይት ፈፃሚ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የተከለከሉ ተግባራት ሚፈፀም የለበትም፡ -**

   1. የምርት ገበያ ደንበኛን ማታለል፣ ማጭበርበር ወይም ማዘናጋት ወይም ለማጭበርበር፣ ለማታለል፣ ወይም ለማወናበድ መሞከር፣
   2. ከምርት ገበያ ወል ጋር በተያያዘ ለደንበኛ ሀሰተኛ ሪፖርት ማቅረብ ወይም እንዲቀርብ ማድረግ፣ ወይም ሀሰተኛ ሚረጃ በማዛገብ ወስጥ ማስገባት ወይም እንዲገባ ማድረግ፣
   3. ከግብይት ወል ጋር የተያያዘ የሸቀጥ ዋጋ የሚጎዳ፣ ወይም ሊጎዳ የሚችል፣ ሀሰተኛ፣ ወይም ሊያሳስት የሚችል ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ሚረጃ ሆነ ብሎ ማሰራጨት ወይም እንዲሰራጭ ማድረግ፣

4. ከምርት ገበያ ወል ጋር በተያያዘ ደንበኛው የተረከባቸውን ወይም በደንበኛው ስም ያፈራቸውን ንብረቶች ወይም ገንዘብ እምነት ማጉደል፣ ማስረቅ፣ ማለወጥ፣

5. በባለሥልጣኑ አዋጅ ወይም መመሪያ መሠረት ዕውቅና የሚያስፈልግ ሆኖ ሳለ ይሄው ሳይፈፀም በአዋጁ ዕውቅና የሚጠይቅ አቋምን መሠረት አድርጎ መንቀሳቀስ፣

6. ይህ ደንብ፣ ማንኛውንም የግብይት ፈጻሚ ዕውቅና ማግኘቱን፣ በሀሰት እንዳይገልጽ ከመከልከል ወጪ ዕውቅና ማግኘቱን የዕውቅናውን አላማና ተግባራት ከመግለጽ አይከለክለውም፡፡ ይሁን እንጂ በማናቸውም ሁኔታ የምርት ግብይት ፈጻሚው በባለስልጣኑ ልዩ ድጋፍ እንዳለው፣ ወይም ተቀባይነት እንዳገኘ ወይም ችሎታው ተመርምሮ እንዳለፈ ማስመሰል፣ ወይም ማከናወን፣

7. የደንበኛውን ገንዘብ ለራሱ ወይም ለሌላ ደንበኛው ማበደር ወይም ከተቀማጭ ሂሳቡ አላማ ወጪ እና ከተቀማጩ ሂሳብ ከፋይ የሆነው ደንበኛ ከተቀማጩ ከክፍያ ጋር በተያያዘ ከሚያደርጋቸው ግብይቶች ውጭ ማጠቀም ወይም ማካፈል፣

8. ሆነ ብሎ ሀሰተኛ ዘገባ ወይም መግለጫ ለባለስልጣኑ፣ ለምርት ገበያው ወይም ለማንኛውም የመንግስት አካል ማቅረብ ወይም እንዲቀርብ ማድረግ፣ ሀሰተኛ ዘገባ በመዝገብ ወስጥ ማስገባት ወይም እንዲገባ ማድረግ፣

**6. ማንኛውም የግብይት ፈፃሚ የባለሥልጣኑ መመዘኛዎች የተሟሉ መሆናቸውን ለሚያጋግጥ ወይም የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓትን አስመልክቶ በባለሥልጣኑ ወይም በምርት ገበያው ለሚከናወኑ ምርመራዎች፣ ፍተሻዎች፣ የኦዲት ሥራዎች፣ ቁጥጥሮች ወይም መገቶች የተሟላና ፈጣን ትብብር ማድረግ አለበት፡፡ እያንዳንዱ የምርት ግብይት ፈፃሚ በባለሥልጣኑ የተሰጡ ትዕዛዞችን ማክበር ይኖርበታል፡፡**

**7. ማንኛውም ግብይት ፈፃሚ በደንበኛው የምርት ገበያ የባንክ ሂሳብ ላይ ከተቀማጭ ሂሳቡ አላማ ውጭ የማዘዝ ስልጣን የለውም፡፡ ማንኛውም የግብይት ፈፃሚ የደንበኛውን ሂሳቦች ለይቶ ማያዝ አለበት፡፡**

**8. ማንኛውም የምርት ግብይት ፈፃሚ ከደንበኛው ወጪ ያሉ ሶስተኛ ወገኖች በፅሑፍ ወክልና/ፈቃድ ካልሰጡት በቀር ከነዚሁ ወገኖች የሚሰጥ ትዕዛዝን መቀበል የለበትም፡፡**

**9. ከሕዝብ ጋር ስለሚደረግ ግንኙነት**

1) ማንኛውም የምርት ግብይት ፈፃሚ፣

/ሀ/ የሚጭበረበር ወይም የሚታለል ወጤት ያላቸው፣

/ለ/ በአቀራረባቸው ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ወይም የተፅዕኖ አካል የሆኑ፣

/ሐ/ በምርት ገበያ ወሎች ንግድ ማካሄድ ለሁሉም ሰው ተገቢ መሆናቸውን የሚያብራሩ ንግግሮችን ለሕዝብ ማድረግ የለበትም፡፡

2) ማንኛውም የምርት ግብይት ፈፃሚ፣

/ሀ/ ሕዝብን ሊያሳስት የሚችል፣

/ለ/ ትክክለኛ ያልሆነ መግለጫ የያዘ ወይም የግብይት ፈጻሚው ሆነ ብሎ የዘለላቸው ገበያን ለማካብ የተዘጋጁ ቁሶችን አሳሳች የሚያደርጉ፣

/ሐ/ የመክሰር አጋጣሚ ስለመኖሩ በአግባቡ መግለጫ ሳይሰጥ የትርፍ ማግኘትን ብቻ የሚያመለክት፣

/መ/ አስቀድሞ የተገኘ ወጤት ለወደፊቱ ወጤት ማግኘት አመላካች አለመሆኑን ሳይጠቅስ በቀዳሚ ጊዜ የተገኘ ትርፍን የሚያመለክት፣

/ሠ/ ገበያን ለመሳብ በተዘጋጁ ማቴሪያሎች /ነገሮች/ በግልጽ በቅስቀሳ ወስጥ የተካተተ በቂ የፍሬ ነገር ማሳ የሌለው እና ተለይቶ በደንብ ያልተገለጸ እና በቂ ሚጃ የሌላቸው ፍሬ ነገሮችን የሚያካትት የቅስቀሳ ሥራ ማካሄድ አይችልም፡፡

10. **ማንኛውም የባለሥልጣኑን መመዘኛ ባለከበረ ወይም በጣሰ የምርት ግብይት ፈፃሚ ላይ በዚህ መመሪያ መሠረት ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል፡፡**

## ክፍል ስምንት
## ስለብሔራዊ የግብይት ፈፃሚዎች ማህበር ዕውቅና

**1. ዕውቅና**

1. ባለስልጣኑ የምርት ግብይት ፈፃሚዎችን ስብዕና፣ ክህሎት፣ የዕውቀት ደረጃን ለማጠበቅና ለማሳደግ ሲል ለብሔራዊ የምርት ግብይት ፈፃሚዎች ማህበር /ከዚህ በኋላ "ማህበር" ተብሎ የሚጠቀስ/ ዕውቅና ሊሰጥ ይችላል፡፡ እንዲህ አይነቱ ማህበር በአዋጁ አንቀፅ 20 መሠረት ዕውቅና ካላገኘ በቀር ሥራውን እንዲጀምር አይፈቀድለትም፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው አጠቃለይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣
   /ሀ/ የምርት ግብይት ፈፃሚዎች፣ የባለሥልጣኑን ወይም የምርት ገበያውን ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ መተዳደሪያ ደንብ ማክበራቸውን ሚጋገጥ፣
   /ለ/ ለግብይት ፈፃሚዎች ወደፊት እና ወዲያውኑ የሚፈጸሙ ወሎችን አስመልክቶ ለምርት ግብይት ፈፃሚዎች የገበያውን አስተማማኝነት እና ሠራተኞቻቸው የምርት ገበያ ሥራዎችን በሚያከናውኑበት ጊዜ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲያደርጉ ማገዝ፣
   /ሐ/ ለምርት ግብይት ፈፃሚዎች የጥብቅና አገልግሎት ማስጠት እንደዚሁም በምርት ግብይት ፈፃሚዎች እና በባለሥልጣኑ መካከል እንደ አገናኝ ድልድይ ሆኖ ማገልገል፣
   /መ/ ከዚህ በላይ በአንቀፅ 2 በተመለከተው መሠረት ሚጀዎችንና ዘገባዎችን እንደዚሁም እንደ አግባቡ በባለሥላጣኑ ወይም በምርት ገበያው የተጠየቁ የምርት ግብይት ፈፃሚዎች ማህበርን የሚመለከቱ ሌሎች ሚጃዎችን ለባለሥልጣኑ ማስጠት አለበት፡፡

**2. የዕውቅና መመዘኛዎች**

**1/ የምዝገባ መግለጫ**

የባለሥልጣኑን ዕውቅና ማግኘት የሚፈልግ ማህበር የምዝገባ መግለጫውን በባለሥልጣኑ በሚዘጋጅ ቅፅ መሠረት ሞልቶ እና ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሚጃዎችና ሠነዶችን አያይዞ እንዲፀድቅ ለባለሠልጣኑ ያቀርባል፡፡

/ሀ/ በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት የተዘጋጁ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ቅደዎች፣ ማሻሻያዎችና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ደንቦችና ሕጎች፣

/ለ/ አደረጃጀትን፣ አባልነትን፣ የሥነ-ሥርዓት ደንቦችንና ሌሎች ለሕዝብ ጥቅም ሲል ባለሠልጣኑ በመመሪያ አስፈላጊ ወይም ተገቢ ናቸው ያለቸውን ሚጃዎች፣

/ሐ/ የስልጠና ደረጃና የብቃት መመዘኛዎችን፣

/መ/ የሚከተሉት የአሠራር ስርዓቶች ማክበራቸውን ለሚጋገጥ የሚደረግ የቁጥጥርና የኦዲት ፕሮግራምን፣

(i) ዝቅተኛ /መነሻ/ ካፒታል፣ ተነጥለው ለየብቻቸው የሚያዙ ሂሳቦች ልዩ ሒሳብ ወይም ሌሎች በምርት ገበያ ተሳታፊዎች ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ መመዘኛዎች፣

(ii) በባለሥልጣኑ ድንጋጌዎች የሚገዙ ግብይቶችን አስመልክቶ የምርት ግብይት ፈፃሚዎችንና ሌሎች ግንኙነት ያላቸውን ሰዎች የንግድ እንቅስቃሴ የሚሞሉ ዝቅተኛ መመዘኛዎች፣

**2/ ባለሥልጣኑ፡-**

/ሀ/ ማህበሩ ለሕዝብ ጥቅም የቆመ እና የዚህን አንቀፅ ድንጋጌዎች የሚያከብር ካልሆነ፣

/ለ/ በማህበሩ የተዘጋጀው ደንብ፣ ማህበሩ ለባለሥልጣኑ እና ለገበያው ሃሳብ እንዲሰጥ እና ማህበሩ ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ባለሥልጣኑና ገበያው ግብይት ፈፃሚው ላይ እርምጃ እንዲወስዱ ሃሳብ ማቅረብ አለበት፡፡ ማህበሩ እርምጃ ለማስወሰድ የወሳኔ ሃሳቡን እና ግኝቱን ለባለሥልጣኑና ለገበያው ካላቀረበ፣

/ሐ/ የምርት ግብይት ፈፃሚዎች የማህበሩ ሕግ ሲወጣ፣ ሲሻሻል ሀላፊወችና ዳይሬክተሮች ሲሾሙ/ሲሚጡ/ እንዲሁም ሌሎች የአስተዳደር ጉዳዮች ሲከናወኑ በቂ ወክልና ስለማግኘታቸው የማህበሩ ደንብ /ሕገ-ደንብ/ የሚያረጋግጥ ካልሆነ፣

/መ/ የማህበሩ ደንብ ምክንያታዊ የሆኑ የአስተዳደር ወጪዎችን ለመሸፈን በምርት ግብይት ፈፃሚዎች መካከል ሚዛናዊ የሆነ የወጪ ድልድል ስለመኖሩ የማህበሩ ደንብ የሚደነግግ ካልሆነ፣

/ሠ/ የማህበሩ ሕገ ደንብ በምርት ግብይት ፈፃሚዎች ላይ በምርት ገበያው ወይም በባለስልጣኑ ስለሚወሰድ የዲስፕሊን ቅጣት አስሜልክቶ የሚቀርብ የወሳኔ ሀሳብ ሚዛናዊ ሥነ-ሥርአት እንደሚከተል የማህበሩ ደንብ የሚደነግግ (ካልሆነ)፣ የምርት ገበያ ፈፃሚው የዲስፕሊን እርምጃ እንዲወሰደበት ወይም እንዳይወሰድበት የሚቀርብ የውሣኔ ሀሳብን ለመወሰን፣ በማንኛወም ሥነ-ሥርዓት ላይ በማህበሩ የሚቀርብ የውሣኔ ሀሳብ ግልፅ የሆነ ክስ እንዲቀርብ፣ የቀረበበትን ክስ የመከላከል ዕድል እንዲያገኝ፣ ምርት ግብይት ፈፃሚው ወይም የሚሟከተው ሰው ክሱን እንዲያወቅ፣ ሂደቱ በመዘገብ እንዲሠፍር፣ የማህበሩ ደንብ የሚደነግግ ካልሆነ በተለይም ውሣኔው፣

(i) የምርት ግብይት ፈፃሚው ያከናወነውን ወይም ሳያከናውን የተወውን ድርጊት የሚያብራራ ፍሬ ነገር፣

(ii) የምርት ግብይት ፈፃሚው አንድን ተግባር በማከናወን ወይም ሳያከናውን በመቅረቱ እንደጣሳቸው የሚቆጠሩ ደንቦች መግለጫ፣

(iii) እንዲፈፀሙ ግዴታ የሆኑ ወይም እንዳይፈፀሙ የተከለከሉ ተግባራትን ተላልፎ ማግኘት የንግድን ርትዕና ፍትሕ መርሆርችን የማያረር ተግባር ተደርጎ እንደሚቆጠር የተቀማጠ መግለጫ፣

(iv) የቅጣት የወሳኔ ሃሳብን የሚያሳይ መግለጫ፣ በዚህ ደንብ ወይም ደንቦች የተከለከሉ ድርጊቶች ወይም ተግባራት ወይም እንዲፈጽሙ የሚፈለጉ ተግባራትን አለሚፈጽም ፍትሐዊ እና ትክክለኛ የሆኑ የንግድ መርሆዎችን እንደመጣስ የሚገልጽ ፍሬ ነገር ካላማላከተ በቀር ለማህበሩ እወቅና አይሰጠውም፡፡

## 3. የማሰማት መብት

ማህበሩ የምርት ግብይት ፈፃሚው እንዲቀጣ፣ እንዲታገድ፣ እንዲሠናበት ለባለስልጣኑ ወይም ለምርት ገበያው ሪፖርት ወይም የወሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ወይም እንዳያቀርብ፣ ወሳኔ በሚሰጥበት ሥነ-ሥርአት ግለሠቡ ጉዳዩን እንዲያወቅ፣ የማሰማት ዕድል እንዲሰጠው፣ ሥነ-ሥርዓቱ በመዘገብ እንዲሰፍር (መዘገብ እንዲደራጅ)፣ ወሳኔው ለዲስፕሊን እርምጃዎች መሠረት የሚሆኑ ምክንያቶችን እንዲያመላክት የማህበሩ ደንብ መደንገግ ይኖርበታል፡፡

## 4. ፍትሐዊ ወክልና

1/ በማህበሩ ቦርድ ወስጥ የተለያየ ፍላጐት ያላቸው ግብይት ፈፃሚዎች እንዲሳተፉ፣ በቂና ትርጉም ያለው ወክልና እንዲያገኙ ዕድል ማስጠት አለበት፡፡

2/ የዲስፕሊን ጉዳይን አስሜልክቶ በሚደረግ ምርመራ፣ ወይም ቅጣት ምዝና ላይ ለማንኛወም ሰው የሚደረግ አግባብ ያልሆነ ማስተንግዶን ወይም አድልኦን ለመከላከል እና ፍትሀዊነትን ለሚረጋገጥ ማህበሩ በዋና ዋና የዲስፕሊን ኮሚቴዎች ላይ የተለያዩ የምርት ግብይት ፈፃሚዎች እንዲሳተፉ መወሰን አለበት፡፡

## 5. ዕወቅናን ስለማፈግ

በባለስልጣኑ ዕወቅና ለማግኘት በአዋጁ አንቀፅ 23 መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት የዚህ ክፍል መመዘኛዎች ማሟላታቸውን በሚረጋገጥ ዕወቅናወን ሊሰጥ ይችላል፡፡ መመዘኛዎቹ ያልተሟሉ ስለመሆኑ አሜልካቹ እንዲያወቅና በቂ የመሠማት ዕድል እንዲያገኝ ከተደረገ በኋላ ባለስልጣኑ በዚህ ክፍል የተማላከቱት መመዘኛዎች ያልተሟሉ መሆናቸውን ከተረዳ ዕወቅናወን ሊከላከል ይችላል፡፡

6. **ዕውቅናን ስለማገድ**

ባለስልጣኑ የአሜካች ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የባለስልጣኑን መመዘኛ ያላሟላ መሆኑን እንዲያውቅና የማሻሻ ዕድል ከተሰጠው በኋላ መመዘኛዎች ያልተሟሉ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ዕውቅናውን ማገድ ይችላል፡፡ ዕገዳው የማህበሩ ደንቦች በባለሥልጣኑ ማስፈርቶች መሠረት መሟላታቸው እስከረጋገጥ ድረስ የፀና ይሆናል፡፡

7. **ዕውቅናን ስለማንሳት እና ለማንሳት ማስታወቂያ ስለማስጠት**

ማህበሩ ባለስልጣኑ ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ያገኘውን በቂ ማስታወቂያ በማስጠት እና ባለስልጣኑ በመወሰው በወሰነው ቅፅ መሠረት የተዘጋጀ የዕውቅና መተው የፅሑፍ ማስታወቂያ ለባለስልጣኑ በማቅረብ ዕውቅናውን መተው ይችላል፡፡

8. **ማህበሩ የዲስፕሊን እርምጃ ለመውሰድ የውሳኔ ሃሳብ የሚቀርብበትን ሥነ-ሥርዓት ለመመርመር ባለሥለጣኑ ስላለው ሥልጣን**

ባለስለጣኑ የማህበሩን ደንቦችና ሥነ-ሥርዓቶች በተሟላ፣ ሚዛናዊ፣ ገለልተኛ እና ውጥ በሆነ አኳኋን እንደዚሁም ከአዋጁ ወይም በባለስልጣኑ ወይም በምርት ገበያው በተደነገጉ መመሪያዎችና ከተሰጡ ትዕዛችና ደንቦች ዓላማ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ለመወሰን ሥነ-ሥርዓቶቹንና አፈፃፀማቸውን ይመረምራል፡፡

9. **የማህበሩ ደንብ ተጨማሪዎች**

1/ ባለስልጣኑ ለሕዝብ ጥቅም ሲል ማንኛውም ጉዳይን የሚመለከቱ ደንቦችን እንዲያሻሽል ወይም ተጨማሪ ደንቦችን እንዲያወጣ ማህበሩ በፅሑፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2/ ማህበሩ በበቂ ጊዜ ወስጥ ማሻሻያውን ካላደረገ ወይም ተጨማሪ ደንቦችን ሳያወጣ በቀረ ጊዜ ደንቡን ማሻሻሉ ወይም ተጨማሪ ደንብ ማውጣቱ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ ከተገኘ፣ እንደዚሁም ለማህበሩ ተገቢው ማስታወቂያ እንዲሰጠው እና የማሻሻ ዕድል እንዲያገኝ ከተደረገ በኋላ ባለስልጣኑ በጠየቀው ጥያቄ መሠረት የማህበሩን ደንብ በትዕዛዝ ለማለወጥ ወይም ተጨማሪ ደንብ ለማውጣት ሥልጣን አለው፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## በባለሥልጣኑ ስለሚደረጉ ምርመራዎች

1. **ወሰንና ተፈፃሚነት**

ይህ ክፍል በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 6(10) እና 7(3) መሠረት ከምርት ግብይቱ ወይም ከተያያዙ ሥራዎች ቁጥጥር አንፃር የሕግ ጥሰቶች መኖራቸውን ለማረጋገጥ በባለሥልጣኑ ወይም በሠራተኞቹ የሚደረጉ ምርመራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ እዚህ ወስጥ በተለየ ሁኔታ ከተገለፀት በስተቀር ድንጋጌዎቹ ወይም ደንቦቹ በምርመራ ሥራዎች ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡

2. **ምርመራውን የሚያደርገው ባለሥለጣን**

1/ የሕግ አስከባሪው ዲፓርትመንት ("ዲፓርትመንቱ") ዳይሬክተር እና በእርሱ ሥልጣን የተሰጣቸውና በእርሱ የሚመሩ የባለሥልጣኑ ሠራተኞች ማንኛው ሰው በምርት ገበያው እና በባለሥልጣኑ አዋጆች ወስጥ የተካተቱትን ድንጋጌዎችና እነዚህን አዋጆች መሠረት አድርገው በወጡ መመሪያዎችና ደንቦች የተመለከቱት ድንጋጌዎች መጣሳቸውን፣ እየተጣሱ መሆናቸውን፣ ሊጣሱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተገቢ ነው ተብሎ ሲወሰን ምርመራዎች ሊያካሂዱ ይችላሉ፡፡ ለዚህ የምርመራ ዓላማም ዳይሬክተሩ በባለሥልጣኑ በሕግ ዕውቅና እንዲሰጣቸው ከሚያስፈልጋቸው ሰዎች ላይ ባለው የመመርመር ሥልጣን በማጠቀም ወይም በባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ሲፈቀድለት መጥሪያዎችን በማውጣት፣ በፈቃደኝነት ከተሰጡት ቃሎች እና መግለጫ ወይም ማስረጃ ሊያሰባስብ ይችላል፡፡

2/ ዳይሬክተሩ የምርመራውን ውጤትና ለባለሥልጣኑ የሚቀርበውን ተገቢ ነው ብሎ የሚገምተውን የሕግ ማስከበር እርምጃ የውሳኔ ሀሳብ ለዋና ዳይሬክተሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፡ በልዩ ሁኔታዎች የክፍያና የአገናኝ ቁጥጥር ዲፓርትመንቱ ዳይሬክተር፣ ዋና የኢኮኖሚ ትንተና ኃላፊው፣ የገበያ ቁጥጥሩ ዲፓርትመንት ዳይሬክተር እና በተሰጣቸው የኃላፊነት ወሰን የሚንቀሳቀሱ ባልደረቦቻቸው በነዚህ ደንቦች መሠረት ምርመራ ለማድረግ እንዲሁም ለባለሥልጣኑ ስለ ምርመራው ውጤት ሪፖርት ለማድረግና የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ ይችላሉ፡፡

3/ በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ ካልሆነ በቀር በምርመራ መጥሪያ መሠረት የተገኙ በሆኑም ባይሆኑም በምርመራ ሂደቱ የተገኙ ማናቸውም ሚስጥሮችና ሰነዶች እንዲሁም ሁሉም የምርመራ ሂደቶች በባለሥልጣኑ ሠራተኞቹ ለሕዝብ ይፋ አይደረጉም፡፡

/ሀ/ ምርመራው ለሕዝብ እንዲገለጽ ባለስልጣኑ ሲያዝዝ ወይም ሲፈቅድ፣

/ለ/ በዳኝነት ሂደቱ ምክንያት ሚስጥሮቹ ወይም ሰነዶቹ ለሕዝብ ክፍት በሆኑ መዝገቦች ሲቀመጡ፡

## 3. መጥሪያ

1/ በባለሥልጣኑ፣ የባለሥልጣኑ ባልደረባ ወይም በአንድ የምርመራ ሂደት ላይ መጥሪያ እንዲያወጣ በባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ሥልጣን የተሰጠው የባለሥልጣኑ ቦርድ አባል፣ በመጥሪያው ላይ ስሙ የተጠቀሰው ግለሰብ ከምርመራው ጋር በተያያዘ አንድ ስሙ በተጠቀሰ ሰው ፊት ተለይቶ በተገለፀ ሰዓት እና ቦታ ቀርቦ ምርመራ እየተደረገበት ያለን ጉዳይ በተመለከተ እንዲመሰክር ወይም የሰነድ ማስረጃ እንዲያቀርብ ወይም ሁለቱንም እንዲፈፅም መጥሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

2/ በአንድ የምርመራ ሂደት መጥሪያ እንዲያወጣ ለአንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሆኑት ሠራተኞች ወይም የባለሥልጣኑ የቦርድ አባላት የሚፈቅድ የባለሥልጣኑ ትዕዛዝ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡፡

/ሀ/ ስለ ምርመራው ስፋት ወይም ወሰን አጠቃላይ መግለጫ

/ለ/ ምርመራውን ለማከናወን መነሻ የሆነውን ሥልጣን፣ እና

/ሐ/ መጥሪያዎቹን ለማውጣት በባለሥልጣኑ ሥልጣን የተሰጠው የባለሥልጣኑ ባልደረባ ማንነት፡፡

3/ ለምርመራው ተግባር የወጡ መጥሪያዎች የሚሰጡት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይሆናል፡፡

/ሀ/ መጥሪያዎች ለተፈጥሮ ሰዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊሰጡ ይችላሉ፡ -

(i) ለግለሰቡ በእጅ በማስጠት፣

(ii) በቢሮው ወይም በመኖሪያ ቤቱ ላለው ኃላፊ ሰው በማስፈረሚያ በማስጠት፣

(iii) ሚጩሻ በታወቀው አድራሻው መሠረት የተመዘገበ ወይም የተረጋገጠ ደብዳቤ በመላክ፣

(iv) መጥሪያው በትክክል ሊደርሰው በሚችልበት በሌላ ዘዴ፡

/ለ/ መጥሪያው የወጣው ሕጋዊ ሰውነት ላለው አካል /ተቋም/ ድርጅት ከሆነ በሚከተሉት መንገዶች ሊሰጥ ይችላል፡፡

(i) በዚህ የሕግ ሰውነት ባለው አካል የሚሠራ ሠራተኛን፣ ዳይሬክተርን ወይም ወኪልን በማስፈረምና በማስጠት፣

(ii) ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ወኪሎች የሚጩሻ አድራሻ አማካኝነት የተመዘገበ ወይም የተረጋገጠ ደብዳቤ በመላክ፣

(iii) ለእነኚህ ወኪሎች መጥሪያው በትክክል ሊደርሳቸው በሚችልበት በማናቸውም ሌሎች ዘዴዎች፡፡

4/ ባለሥልጣኑ በሚወስነው ማጠን መሠረት በመጥሪያ ለሚቀርቡ ምስክሮች ክፍያ ይሰጣቸዋል፡፡

## 4. የምክርነት ቃሎችን በጽሑፍ ስለማስፈር

በምርመራ ሂደቱ የምስክርነት ቃል በመደበኛ ሪፖርተር ወይም በሌላ ሰው ወይም ምርመራውን በሚያካሂዱ የባለሥልጣኑ ባልደረቦች ሠራተኞች፣ ወይም ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው ሌላ ዘዴ በጽሑፍ ይመዘገባል፡፡

**5. ቃለ መሃላ፣ የሐሰት ቃል፣ የወንጀል ድርጊቶችን ስለማሳወቅ**

1/ በባለሥልጣን መ/ቤቱ አባል ወይም ምርመራውን በሚያደርገው ባልደረባ ፍቃድ የምስክርነት ቃል በቃለ መሃላ ሊወሰድ ይችላል፡፡

2/ በባለሥልጣኑ የምርመራ ሂደት ውስጥ ሀሰተኛ ቃል በቃለ መሃላ የሚሰጥ ማንኛውም ሰው በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ በቃለ መሃላም ሆነ ወይም ያለ ቃለ መሃላ እያወቀና ሆን ብሎ ሀሰተኛ ወይም የሚያሳስል ቃል የሚሰጥ ወይም አንድ መሠረታዊና ወሳኝ የሆነ ፍሬ ነገርን ወደ ሀሰትነት የሚቀይር፣ የሚደብቅ ወይም የሚሸፋፍን ወይም ሀሰተኛ፣ የፈጠራና የተጭበረበረ ሚዛን መሆኑን እያወቀ ሀሰተኛ ጽሑፍ ወይም ሰነድ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

3/ በምርት ገበያ ባለሥልጣኑ አዋጅ የተመለከተ ማንኛውም የወንጀል ድርጊት ወይም በምርመራ ሂደቱ የተገኘ ሌላ የወንጀል ድርጊት ለሚመለከታቸው የፍትሕ አካላት ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፡፡

**6. የምስክሮች መብቶች**

1/ በአንድ ምርመራ የሰነድ ማስረጃ እንዲያቀርብ ወይም የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ መጥሪያ የደረሰው ማንኛውም ሰው በራሱ ጥያቄ መሠረት ባለሥልጣኑ መጥሪያ በስሙ እንዲወጣ የወሰነበትን ትዕዛዝ ሰነድ ለመመርመር ይፈቀድለታል፡፡ ሆኖም የትዕዛዙን ሰነድ ይዞ ሊያቆይ አይችልም፡፡ ነገር ግን የትዕዛዝ ሰነዱን ቅጂ የዞ ሊያቆይ የሚችለው ኃላፊነት ላለው የባለሥልጣኑ ባልደረባ የሰነዱን ቅጂ ይዞ በማቆይበት ወቅት በምርመራው ሂደት ውስጥ ያሉ ሰዎችን የግል መብት ከማጠበቅ እና የምርመራው ሂደት እንዳይስተጓጎል ከማድረግ ዓላማ አንፃር የሚጋጭ መሆኑን በአጥጋቢ ሁኔታ ካረጋገጠ ብቻ ነው፡፡

2/ በምርመራ ሂደቱ ሚዛን ወይም ማስረጃ እንዲያቀርብ የተጠየቀ ሰው የሰጠውን የምስክርነት ቃል መዝገብ ይዞ ለማቆየት ወይም ለሬከርድ አገልግሎቶች በወጡ የክፍያዎች ሰንጠረዥ የተመለከቱትን ክፍያዎች ከከፈለ ቃሉ የተፃፈበትን መዝገብ ወይም ቅጂ ለማግኘት ይችላል፡፡ ሆኖም በቂ ምክንያት ሲኖር ምስክሩ ትክክለኛውንና ሕጋዊ የሆነውን ጽሑፍ ብቻ በመመልከት ብቻ እንዲወሰን ሊያደርግ ይችላል፡፡

3/ በምርመራው ወቅት በባለሥልጣኑ ወይም በባለሥልጣኑ ባልደረባ ጥያቄ ወይም ፈቃድ በአካል የሚቀርበው ሰው የሕግ አማካሪውን ይዞ መምጣት፣ ወይም በአማካሪው መወከል ወይም ከአማካሪው ምክር ማግኘት ይችላል፡፡ አማካሪውን ይዞ የመምጣት፣ በአማካሪ የመወከል እና ከአማካሪ ምክር የማግኘት መብት ማለት በየትኛውም ከምርመራው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ሂደት ቃሉን የሚሰጠው ሰው ከጠበቃ ጋር የመገኘት መብት፣ እንዲሁም ከምርመራው በፊት በምርመራ ላይ እያለ እንዲሁም ምርመራው ሲያልቅ የዚህን ጠበቃ ምክር የማግኘት መብት ማለት ነው፡፡

4/ ለምስክሮች መብቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት፣ ባለሥልጣኑ በቂ ምክንያት ሲኖር አንድ ጠበቃ የምርመራ ሂደቱን በሚደናቀፍ ተግባር ተሰማርቶ ካገኘው ከምርመራው ሂደት ሊያግደው ይችላል፡፡ ምርመራውን የሚያካሂደው ሰው አንድ ጠበቃ የማዘግየት፣ የማስተጓጎል ወይም ያለመታዘዝ ባህርይ በሚያሳይበት ጊዜ ለባለሥልጣኑ ይህንኑ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡ ለጠበቃው አስፈላጊው ማስታወቂያ ከተሰጠው በኋላ ባለሥልጣኑ በምርመራው ወቅት ስለጠበቃው ባህርይ የሚያስረዱ የጽሑፍ መዝገቦች ወይም ሌላ ተመሳሳይ ወይም ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው ወይም በሚያዘው መሠረት በሚቀርብ ተጨማሪ የጽሑፍ ወይም የቃል መግለጫ ላይ በመመስረት ሁኔታዎች በሚፈቅዱት መሠረት እርምጃዎችን መወሰድ ይችላል፡፡

5/ በምርመራ ወቅት ቃሉን ወይም ሌላ ሚረጃ የሚሰጥ ምስክር በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መሠረት ባለው ራስን ከመወንጀል የማጠበቅ መብት የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች አለመመለስ ይችላል፡፡

**7. የምስክሮች ተለይቶ መቀመጥ**

1/ ምርመራውን በሚያካሂደው ሰው ውሣኔ ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ምስክሮች እና ምስክሮች ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች ሌሎች ምስክሮች በሚመረመሩበት ወቅት እንዲገኙ አይፈቀድላቸውም፡፡

2/ በምርመራ ወቅት ጠበቃው ከአንድ በላይ በሆኑ ምስክሮች በመወከሉ ምክንያት የምርመራ ሂደቱን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሊያዛባ ወይም ሊያደናቅፍ ይችላል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖር መርመራውን የሚያካሂደው የባለሥልጣኑ ባልደረባ ጠበቃው ለሚደግፈው ጠበቃ ከሆነለት ምስክር ውጭ ሌሎች ምስክሮች ቃላቸውን ሲሰጡ እንዳይገኝ ሊከለክለው ይችላል፡፡ አስከሚቻለው ድረስ እና የመርመራ ሂደቱን በማይናጋ መልኩ ጠበቃው ለምን እንደተከለከለ ሊገለጽለት ይችላል፡፡

**8. የሕግ ማስከበር የውሳኔ ሃሳብ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት**

**1/** ዲፓርትመንቱ በራሱ ውሣኔ በሕግ ማስከበር ሂደት ክስ ውስጥ ስማቸው ለተጠቀሱ ሰዎች አነሱን በተመለከተ ስለቀረቡ ክሶች ምንነት ሊነግራቸው ይችላል፡፡ ዲፓርትመንቱ የተጠቀሱት ሰዎች ባለሥልጣኑ በባልደረባው የቀረበለትን የክርክር ሂደት መጀመር የውሣኔ ሃሳብ ከመመርመሩ በፊት የጽሑፍ መግለጫ እንዲያቀርቡ ለመጋበዝ ይችላል፡፡ በሌላ ሁኔታ በዲፓርትመንቱ ዳይሬክተር ካልተወሰነ በስተቀር የጽሑፍ መግለጫው ዲፓርትመንቱ በገለፀላቸው በ14 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

**2/** በዲፓርትመንቱ ዳይሬክተር በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር እነዚህ የጽሑፍ መግለጫዎች ዲፓርትመንቱ እነሱን በሚመለከት ስለቀረቡ ክሶች ምንነት በነገራቸው በ14 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለባቸው፡፡ የጽሑፍ መግለጫዎቹ ከ20 ገጽ የማይበልጡ ሆነው በኤ4 ወረቀት በሁለት መስመር ክፍተት መፃፍ አለባቸው፡፡ መግለጫው ከሕግ ማስከበር ሂደቱ አጀማመር ጋር አግባብነት ያላቸውን የፍሬ ነገር፣ የሕግና የፖሊሲ ጉዳዮች አስተያየቶቻቸውን ማቅረብ አለባቸው፡፡ በሚቀርበው መግለጫ ላይ የተመለከቱትን ፍሬ ነገሮች በግል የሚያውቃቸው ሰው ፍሬ ነገሮቹን በተመለከተ የተፃፉትን መግለጫዎች በቃለ መሃላ ሚያረጋግጥ አለበት፡፡ ለዲፓርትመንቱ ዳይሬክተር የሚሰጡ መግለጫዎች ምርመራውን ለሚያደርገው ሰራተኛ ኮፒ በማድረግ ስለ ምርመራው ዓይነት በግልፅ ማመልከት አለባቸው፡፡ በተጨማሪ መግለጫዎቹ ለባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ እንዲደርሱ የሚጠይቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**3/** በተመሣሣይ ሁኔታ በምርመራው ሂደት የሚሳተፉ በራሳቸው ተነሳሽነት የጽሑፍ መግለጫ የሚያቀርቡ ሰዎች ከላይ የተመለከቱትን አግባብ ያላቸውን የሥነ-ሥርዓት ደንቦች መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ ዲፓርትመንቱ የህግ ማስከበር ክስ ሂደት በባለሥልጣኑ መጀመር አለበት የሚል ሃሣብ ካለው ባለሥልጣኑ ሲጠይቅ ማንኛውም የጽሑፍ መግለጫ መላክ ይኖርበታል፡፡ ባለሥልጣኑ ባለው ሥልጣን በባልደረቦቹ የተሰጠትን የህግ ማስከበር ክስ ሂደት መጀመር የውሣኔ ሃሣብ ሲመረምር የቀረቡለትን መግለጫዎች በሙሉ ወይም በከፊል ከግምት ሊያስገባው ወይም ከናካቴውም ላይጠቀምበት ይችላል፡፡

**9. የምርመራ ሪፖርት**

1/ የባለሥለጣኑ የሕግ ማስከበር ባልደረባ ጥሰት ለመኖሩ በቂ ምክንያት አለ ብሎ በሚያምንባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ለባለሥልጣኑ የሕግ ማስከበር ዳይሬክተር የጽሑፍ የምርመራ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡ የምርመራ ሪፖርቱም ምርመራው የተጀመረበትን ምክንያት፣ ካለም የክስ አቤቱታውን አጭር መግለጫ አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች፣ የሕግ ማስከበር ባልደረባ ማጠቃለያ እና የሕግ ማስከበር ዲፓርትመንት የጉዳዩ ሂደት መቀጠል ይኖርበት እንደሆነ ያለውን የውሣኔ ሃሣብ የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

2/ ከምርመራው በኋላ የሕግ ማስከበር ባልደረባ ጥሰት ስለመኖሩ በቂ ምክንያት የለም ብሎ ሲወስን ምርመራው የተጀመረበትን ምክንያት፣ ካለም የክስ አቤቱታውን አጭር መግለጫ አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች፣ እና የሕግ አስከባሪውን የድምዳሜ ሃሣብ የያዘ የጽሁፍ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡ ሪፖርቱ የምርመራ መዝገቡ አካል ከሆነ በኋላ ምርመራው ሊዘጋ ይችላል፡፡

3/ የባለሥልጣኑ ሕግ ማስከበር ባልደረባ ምርመራ ለሚደረግበት ሰው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲፃፍለት ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም ጥሰት ስለመኖሩ አመላካች ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) በተደነገገው መሠረት በሚፈለገው የምርመራ ሪፖርት ውስጥ በሕግ ማስከበር ባልደረባ የወጣው ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ቅጂ መካተት አለበት፡፡

**10. የምርመራ ሪፖርቱን ስለመገምገም**

1/ የሕግ አስከባሪው ዳይሬክተር በአንቀጽ 9 መሠረት የሚቀርብለትን እያንዳንዱን የምርመራ ሪፖርት ወዲያውኑ ማየት አለበት፡፡ ዳይሬክተሩ ተጨማሪ ምርመራ ወይም ማስረጃ ያስፈልጋል ብሎ ካመነ የሕግ አስከባሪው ባልደረባ ተጨማሪ ምርመራ እንዲያደርግ ወዲያውኑ ትዕዛዝ ይሰጠዋል፡፡

2/ የተሟላ የምርመራ ሪፖርት በደረሰው ከ15 ቀናት በማይበልጥ ተገቢ ጊዜ ውስጥ ዳይሬክተሩ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን እርምጃ ይወስዳል፣

ሀ/ ጥሰት ስለመኖሩ በቂ ምክንያት ከሌለ ወይም ጉዳዩን ለማየት አስተማማኝ መሠረት ከሌለ ሌሎች ቀጣይ እርምጃዎች እንዳይወሰዱ ሊያዝ ይችላል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ውሳኔ በጽሑፍ ሆኖ ምክንያቶቹን የሚገልፁ ዐረፍተ ነገሮች ማያዝ አለበት፡፡

/ለ/ የሕግ ጥሰት ስለመኖሩ በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን የሕግ አስከባሪው ዳይሬክተር በዚሁ ክፍል አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የውሳኔ ሃሳብ አቅርቦ ይሁንታ ሲያገኝ ጉዳዩ ለአስተዳደራዊ ችሎት ቀርቦ ይታይ ዘንድ ባለስልጣኑን በመወከል ክስ እንዲመሰረት ያደርጋል፡፡

3/ ባለስልጣኑ የሕግ ጥሰት የተፈፀመ መሆኑን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ፣ ሆኖም በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የሕግ ጥሰቱ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ በአሥር ዓመታት ውስጥ ለአስተዳደራዊ ችሎቱ ክስ ካላቀረበ ክስ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

**11. ጊዜያዊ የእግድ ትዕዛዝ**

1/ ምርመራው እንዲካሄድ ካስደረገ በኋላ ባለሥልጣኑ ማንኛውም ሰው የባለሥልጣኑን አዋጅ ወይም አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ መመሪያዎችን ድንጋጌዎች ጥሶ ከተገኘ ወይም ሊጥስ ከሆነ የተጠቀሰው ሰው የተባለውን ድርጊት ከመፈፀም እንዲገታ ትዕዛዝ ሊሰጠው ይችላል፡፡

2/ የሕግ ሰውን የሚመለከት ትዕዛዝ የግል ድርጊታቸውን ለመግታት በሚፈለገው ህጋዊ ሰው ራሱና በሁሉም አባላቱ፣ የስራ ኃላፊዎች እና ዳይሬክተሮች ላይ የጸና ይሆናል፡፡

## ክፍል አሥር

## በባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ ችሎት የጉዳዮች አወሳሰን ሥነ ሥርዓቶች

**1. አስተዳደራዊ ችሎት**

በባለሥልጣኑ የሚቋቋመው አስተዳደራዊ ችሎት ጥሰቶች መፈፀማቸውን ወይም አለመፈፀማቸውን እንዲሁም ተገቢ የሆኑ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ይወስናል፡፡

**2. የአስተዳደር ችሎት ስልጣንና ተግባራት**

1/ በባለሥልጣኑ አዋጅ አንቀጽ 6(10) እና 7 መሠረት የባለሥልጣኑ የአስተዳደር ችሎት የምርት ግብይቱንና ከምርት ግብይቱ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚዛዙ ሕጎች መጣስን ተከትሎ የሚቀርቡለትን ጉዳዮች በሚከተሉት ሥነ ሥርዓቶች መሠረት አይቶ የመወሰን ስልጣን ይኖረዋል፡፡

2/ አስተዳደራዊ ችሎቱ ፍትሐዊና ሥርዓቱን የጠበቀ የክርክር ሂደት ይረጋገጥ ዘንድ ኃላፊነት ሲኖርበት የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፡ -

/ሀ/ ቃለመሃላዎችንና ሚረጋገጫዎችን ማስፈፀም፣
/ለ/ መጥሪያዎችን ማውጣት፣
/ሐ/ በማስረጃ ተቀባይነት ላይ መወሰን፣
/መ/ ተገቢ ማስረጃን መቀበል፣
/ሠ/ ምስክሮችን መመርመር፣
/ረ/ የክስ ማስማት ሂደቱን መቆጣጠር፣
/ሰ/ የሚነሱ ሜቸወንም ጉዳዮች መርምሮ ብይን ማስጠት፣
/ሸ/ ውሣኔ ማስጠት፣ እና
/ቀ/ በአስተዳደራዊ ችሎቱ የተሰጠውን ትዕዛዝ ያላከበረ ወገን ወይም ወኪል ላይ አግባብነት ያለውን እርምጃ መውሰድ፡፡

## 3. የሥራ ክፍፍል

1/ አስተዳደራዊ ችሎቱ የዳኝነት ሥራውን ወይም ኃላፊነቱን ሲወጣ ለባለሥልጣኑ ሠራተኞች፣ ተቀጣሪዎች ወይም ወኪሎች ተጠሪ አይሆንም፡፡ በእነሱ ቁጥጥር ወይም አሜራር ሥርም አይሆንም፡፡

2/ በአንድ ጉዳይ የምርመራ ወይም የክስ ሥራ ላይ ያለ ማንኛውም የሥራ ኃላፊ፣ ሠራተኛ፣ ወይም የባለሥልጣኑ ወኪል በሂደቱ ምስክር ወይም አማካሪ ከሚሆን በስተቀር ከክሱ ሂደት ጋር በተያያዘ ወይም ከዚሁ የክስ ሂደት ጋር በፍሬ ነገር ጉዳይ ተመሳሳይነት ባለው የሌላ የክስ ሂደት ተሳታፊ ከሆነ ሜልስ ሰጪዎች በጽሑፍ ካልፈቀዱ በስተቀር በአስተዳደራዊ ችሎቱ ወይም በባለሥልጣኑ የውሣኔ ሂደት ሊሳተፍ ወይም ምክር ሊሰጥ አይችልም፡፡

## 4. ከዳኝነቱ ራስን ስለ ማግለል

አንድ የአስተዳደሩ ችሎት ዳኛ አድልኦንና የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ ወይም በተመሣሣይ ምክንያቶች በሂደቱ በዳኝነት መቀጠል እንደማይችል ከወሰነ ራሱን ከዳኝነት ለማግለል ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ ለባለሥልጣኑና ለእያንዳንዱ ወገን ከዳኝነት ራሱን ማግለሉንና ምክንያቱን ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 5. አስቀድመው የተወሰኑ አስተዳደራዊ ቅጣቶች

ባለሥልጣኑ እያንዳንዱን የደንብ መጣስ አስመልክቶ የሚወሰዱ ከፍተኛ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ወሰን የሚደነግግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡ የባለሥልጣኑ ድንጋጌዎች ቀድመው የተወሰኑ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን የያዙ ከሆነ የአስተዳደራዊ ችሎቱ በእያንዳንዱ በቀረበለት ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ ሚድረጉ የራሱ ምርጫ ይሆናል፡፡ እነዚህ አስቀድመው የተደነገጉ የአስተዳደር ቅጣቶችን ተፈፃሚ ለማድረግ በክሱ ላይ መጠቀስ አለባቸው፡፡ በዚህን ጊዜ የቀረበውን ክስ የካደው ተጠሪ በክሱ ላይ የተመለከተውን ጥሰት በክሱ ማስማት ሂደት ሜፈፀሙ ከተረጋገጠ አስተዳደራዊ ችሎቱ አስቀድመው የተወሰኑ አስተዳደራዊ ቅጣቶች ወይም ሌሎች ተገቢ አነስተኛ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ሊጥል ይችላል፡፡

## 6. ስለ ክሶች

ክሶች የሚከተሉትን ማያዝ አለባቸው፣

1/ የተጠረጠረው ሰው ፈፅሟቸዋል የተባሉ ድርጊቶች፣ ምግባሮች ወይም ተግባሮች፣
2/ የተጣሰውን ድንጋጌ ወይም ሊጣስ የተቃረበውን ድንጋጌ፣
3/ አስቀድሞ የተቀመጠ አስተዳደራዊ ቅጣት ካለ፣ ይህንኑ፣
4/ ክሱ እንዲሰማ የሚቀርቡ አቤቱታዎች መቼ እንደሚቀርቡ፣ እና
5/ ክስ ለቀረበበት ሰው የሚሰጥ የሚከተለውን ምክር፡

ሀ/ ክርክሩ እንዲሰማ የመጠየቅ መብት እንዳለው፣
ለ/ ክሱ እንዲሰማ በተወሰነው ቀን ያለበቂ ምክንያት ካልተገኘ ክርክሩ እንዲሰማለት ያለውን መብት እንደተወው እንደሚቆጠር፣

ሐ/ ለቀረበበት ክስ በግልጽ በሚተባበል ሜለስ ካልሰጠ የቀረበበበትን ክስ እንዳመነ እንደሚቆጠር፡፡

7. **የመከለል መብት**

ተጠሪው የክሱ ወረቀት እንደደረሰው የተፈጥሮ ሰው ከሆነ በአካል የሕግ ሰው ከሆነ ደግሞ ሥልጣን በተሰጠው ወኪሉ አማካኝነት መቅረብ ወይም በሁሉም ቀጣይ የክርክሩ ሂደቶች በሕግ ጠበቃ መከለል ይችላል፡፡

8. **ለክሱ የሚሰጡ ሜለሶች**

1/ እንደጉዳዩ ሁኔታና ወስብስብነት ተጠሪው ለክሱ ሜለስ የሚሰጥበት ተገቢ ጊዜ ይሰጠዋል፣

2/ ሜለሱ በጽሑፍ ሆኖ ተጠሪው የቀረበበትን ክስ አስሜልክቶ ስለማመኑ፣ ስለመካዱ ወይም ለማመን ወይም ለመካድ በቂ ሚዛኝ የሌለው ስለመሆኑ ወይም ማስረጃ ለማግኘት ስላለመቻሉ መግለጽ አለበት፡፡ በቂ ሚዛኝ ስላለመኖሩ የቀረበው መግለጫ ክሱን የመካድ ውጤት ይኖረዋል፡፡

3/ ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ወስጥ ሜለስ ካልሰጠ የአስተዳደር ችሎቱ የቀረበለትን ክስና ማስረጃ ከህግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር ወሳኔ ይሰጣል፡፡

4/ የቀረበወን ክስ በግልጽ ያለመካድ ክሱን እንደማመን ይቆጠራል፡፡

9. **ክስን ስለማመን ወይም ስለመካድ**

1/ ተጠሪው የቀረበበትን ክሶች ካመነ ወይም ሳይከዳቸው ከቀረ አስተዳደራዊ ችሎቱ በክሱ ላይ የተመለከቱትንና ተጣሱ የተባሉትን ድንጋጌዎች እንደተጣሱ ሊቆጥራቸው ይችላል፡፡

2/ አስተዳደራዊ ችሎቱ ተፈፀሞ ለተገኘው ጥሰት ተነፃፃሪ የሆነ በክሱ ወስጥ የተገለፀ አስቀድሞ ተወስኖ የተደነገገ አስተዳደራዊ ቅጣት ካለ የሚዪበልጠወን አስተዳደራዊ ቅጣት ይጥላል፡፡

3/ አስቀድሞ የወጣ አስተዳደራዊ ቅጣት ካልተገለፀ አስተዳደራዊ ችሎቱ ተፈፀሟል ለተባለው እያንዳንዱ የሕግ መጣስ ተገቢ የሚለወን አስተዳደራዊ ቅጣት ሊወስን ይችላል፡፡

4/ አስተዳደራዊ ችሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 1፣2 እና 3 መሠረት የሚወስደወን አስተዳደራዊ ቅጣት ለተጠሪው ወዲያወኑ በጽሑፍ ያሳወቃል፡፡ ሆኖም በዚህ ጽሑፍ ወስጥ ተጠሪው ተገቢ በሆነ ጊዜ ወስጥ በሚወሰደው አስተዳደራዊ ቅጣት ላይ የማሰማት ዕድል እንዲሰጠው ማጠየቅ እንደሚችል ይገለጽለታል፡፡ ነገር ግን በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 2 መሠረት በሚወሰዱ አስተዳደራዊ ቅጣት ላይ ጉዳዩ እንዲሰማለት ማጠየቅ አይፈቀድለትም፡፡

5/ በባለሥልጣኑ ደንብ ላይ ተጠሪው በማስታወቂያ ጽሑፍ ላይ በተገለፀው ጊዜ ወስጥ ጉዳዩ እንዲሰማለት ካልጠየቀ አስተዳደራዊ ቅጣቱን እንደተቀበለው ይቆጠራል በሚል ሊደነገግ ይችላል፡፡

10. **ክሱን ስለመካድና የማሰማት መብት**

በማንኛወም ጊዜ ሜለስ ሰጪው በተካደ ክስ ላይ ወይም በአንቀጽ 9 ንዐስ አንቀጽ 3 መሠረት በአስተዳደራዊ ችሎቱ በተወሰነ አስተዳደራዊ ቅጣት ላይ የማሰማት ጥያቄዎች በሚያቀርብበት ጊዜ በአንቀጽ 11 ድንጋጌዎች መሠረት የማሰማት ዕድል ይሰጠዋል፡፡ ባለሥልጣኑ በሚያወጣቸው ድንጋጌዎች በቂ ከሆኑ ምክንያቶች ወጪ ማሰማቱ የተካዱ ክሶችን ብቻ እና/ወይም በአንቀጽ 9 ንዐስ አንቀጽ 3 መሠረት በአስተዳደራዊ ችሎቱ የተወሰኑትን አስተዳደራዊ ውሣኔዎችን ብቻ የተመለከተ መሆን ይገባዋል በሚል ሊደነግግ ይችላል፡፡

11. **ችሎት ስለመቅረብና ስለክሱ ማሰማት**

1/ ተከራካሪ ወገኖቹ በአካል ሊቀርቡ ወይም በጠበቃ ሊወከሉ ይችላሉ፡፡

2/ የሚከተሉት ዝቅተኛ ማስፈርቶች በማንኛወም ክስ ማሰማት ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡

/ሀ/ የክሱ ማሰማት ፍትሐዊ መሆንና በአስተዳደራዊ ችሎቱ አባላት ፊትም መካሄድ ይኖርበታል፡፡ የክሱ ማሰማት ሁሉም የአስተዳደር ችሎቱ አባላት ባሉበት ወይም በከፊል በተሰየሙበት ፓናል ሊሰማ ይችላል፡፡ ነገር ግን በሚታየው ጉዳይ ላይ የገንዘብ፣ የግል ወይም ሌላ ጥቅም ካለው ሰው ወይም ድርጅት ጋር ግንኙነት ያለው የአስተዳደር ችሎቱ አባል በችሎቱም ሆነ በፓናሉ ማሰየም አይችልም፡፡

/ለ/ ሜለስ ሰጪው የሕግ አስከባሪው ባልደረባ ክሱን ሲያቀርብ መሠረት ያደረጋቸወንና በባለስልጣኑ እጅ ወይም ይዞታ የሚገኙትን ሁሉንም ማዛግብት፣ ሰነዶች ወይም ሌሎች ተጨባጭነት ወይም ግዘፍነት ያላቸወን ማስረጃዎች ከክሱ ማሰማት በፊት ለመሜልከት ይችላል፡፡

/ሐ/ ለተጠሪው ተገቢው ማስታወቂያ ከተሰጠው በኋላ የክሱ ማሰማት ወዲያወኑ ይጀሜራል፡፡

/መ/ የክሱ ማሰማት የሥነ ሥርዓት ደንቦች የክሱን ፍትሐዊነት በሚያሳጣ መልኩ ኢ-መደበኛ መሆን የለባቸወም፡፡

/ሠ/ የሕግ አስከባሪው ባልደረባ በክስ ማሰማቱ ተከራካሪ ወገን ሲሆን የማሰማቱ ጭብጥ በሆኑት ክሶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶች ላይ ሃሳቡን ያቀርባል፣ ያስረዳል፡፡

/ረ/ ተጠሪው በማሰማት ሂደቱ በምስክርነት ለማቅርበብት ማቸተውም ሰዎች የማቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ መብት አለው፡፡

/ሰ/ ተጠሪው ምስክሮችን የመጥራትና ለክሱ ይጠቅማል ያለውን ማንኛውንም ማስረጃ የማቅረብ መብት አለው፡፡

/ሸ/ ባለሥልጣኑ በምስክርነት የተጠሩ ሰዎች በክስ ማሰማቱ ጊዜ እንዲገኙና ማስረጃ እንዲያቀርቡ ያደርጋል፡፡

/ቀ/ ከሞላ ጐደል የክሱ ማሰማት ሂደት ቃል በቃል ተቀድቶ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ ይህም የክርክሩ ሂደት ማዝገብ አካል ይሆናል፡፡ ቅጂው በትክክል ወደ ጽሑፍ ለለወጥ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን የባለሥልጣኑ ባልደረባ ወይም ተጠሪው ካልጠየቀ በስተቀር ወደ ጽሑፍ ማለወጥ አያስፈልገውም፡፡

3/ የክስ ማሰማት ሂደቱን ቅጅ ወደ ጽሑፍ የማለጥ ሥራ ወጪ በጠየቂው ወገን ይሸፈናል፡፡

4/ አስተዳደራዊ ችሎቱ ድርጊቱ የክስ ማሰማቱን ሂደት ባስተጓጉለ ማንኛውም ሰው ላይ በያዘው መዝገብ ወዲያውኑ ቅጣት ሊጥል ይችላል፡፡

## 12. የክስ ማሰማት ሂደቱ ለህዝብ ግልፅ ስለመሆኑ

ሁሉም የክስ ማሰማት ሂደቶች ለሕዝብ ግልጽ ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን በተጠሪው ወይም ይፋነቱ በሚጐዳው ምስክር ማመልከቻ ማሻነት፣ የንግድ ሚስጥሮቹ ወይም ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው የንግድ፣ የገንዘብ ሚጃዎች ወይም የግል ሕይወት ጉዳዮች ይፋ እንዳይሆኑ ለማጠበቅ ሲባል እስተዳደራዊ ችሎቱ ዳኛ የተወሰኑ ሰነዶች ወይም የምስክርነት ቃሎች ይፋ ባልሆነ ማገድ እንዲሰጡ እንዲያዙ ሊያዝ ይችላል፡፡

## 13. መጥሪያዎች

1/ ተከራካሪ ወገን ማንኛውም ሰው ማስረጃ በሚሰማበት ቀን ቀርቦ ምስክርነት እንዲሰጥ መጥሪያ እንዲወጣለት ለአስተዳደራዊ ችሎቱ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

መጥሪያዎች እንዲወጡ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በሙሉ በጽሑፍ ሆነው ቅጂዎች ያሏቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

2/ አንድ ሰው አንድ ሰነድ ወይም ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ በአንድ በተወሰነ ቦታና ጊዜ እንዲያቀርብ የሚፈልግ ወገን ለዚሁ ሰው መጥሪያ ይጻፍለት ዘንድ ለአስተዳደራዊ ችሎቱ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

መጥሪያ እንዲወጣ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በሙሉ በጽሑፍ ሆነው ቅጂዎች ያሏቸው መሆን አለባቸው፡፡

3/ አስተዳደራዊ ችሎቱ የቀረበለትን የመጥሪያ ማመልከቻ ሲመረምር ማመልከቻው በዚህ ክፍል የተመለከቱትን ጉዳዮች የሚሟላና ተገቢ ያልሆነ ጫና የሚፈጥር፣ ከልክ ያለፈ ያልሆነና ምክንያታዊ የሆነ፣ እንዲሁም አላስፈላጊ ጫና ወይም ሸክም የሚፈጥር እና አስቸጋሪ አለመሆኑን ካረጋገጠ የተጠየቀውን መጥሪያ ያወጣል፡፡

4/ አስተዳደራዊ ችሎቱ የቀረበው የመጥሪያ ማመልከቻ ወይም ይዘቱ ምክንያታዊ ያልሆነ፣ አስቸጋሪ፣ ከልክ ያለፈ ወይም ጫና ወይም ሸክም የሚያስከትል ነው ብሎ ሲያምን መጥሪያ ማውጣቱን ሊከለክል ይችላል፣ ወይም በሚዛናዊነት መርሆዎች በመመራት የተወሰነ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## 14. ማስረጃዎችን ስለመመዝገብ

ማስረጃ ለመቀበል የሚደረገው የማሰማት ሂደት በአስተደደራዊ ችሎቱ የበላይ ተቆጣጣሪነት በችሎቱ ፀሐፊ ይመዘገባል፣ በጽሑፍም ይያዛል፣

የመጀመሪያው በጽሑፍ የተያዘው መዝገብ የሪኮርዱ አካል በመሆን ብቸኛ ሕጋዊ መዝገብ ይሆናል፡፡

## 15. ክስን ስለማዘጋት

አስተዳደራዊ ችሎቱ በተጠሪው ላይ ሊቀርብ የሚችል ክስ የለም ብሎ ሲወስን ጉዳዩን ይዘጋዋል፡፡

## 16. ክስን ስለማንሳት

የሕግ አስከባሪው ዳይሬክተር ከባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ጋር ከተማከረ በኋላ አስተዳደራዊ ችሎቱ ወሳኔ ከማስጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ በርሱ ፊርማ የተረጋገጠ የጽሁፍ ማመልከቻ በማቅረብ ወይም በህግ አስከባሪው ባልደረባ በኩል እንዲቀርብ በማድረግ ክሱን ሊያነሳ ይችላል፡፡

## 17. የአስተዳደራዊ ችሎቱ ውሳኔ

በአንቀጽ 11 መሠረት የተደረገውን የክስ ማሰማት ሂደት በማከተልና በሂደቱ በሪኮርድነት የተመዘገበውን የማስረጃ ክብደት መሠረት በማድረግ የአስተዳደር ችሎቱ በጽሑፍ የተዘጋጀ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ የዚህን ውሳኔ ቅጂም ለተጠሪው ይሰጣል፡፡ ውሳኔውም የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡፡

1/ ክሶችን ወይም ስለ ክሶቹ አጭር መግለጫ

2/ ለክሶች የተሰጠ ምላሽ ወይም የምላሹ አጭር መግለጫ

3/ ክሱ ሲሰማ የቀረቡ ማስረጃዎች አጭር መግለጫ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በምርመራ ሪፖርቱ ላይ የተመለከተውን በማጣቀስ ማካተት፣

4/ ተጠሪው የጣሰውን ድንጋጌ ጨምሮ በእያንዳንዱ ክስ ላይ የተሰጡ ግኝቶችና ድምዳሜዎችን የያዘ መግለጫ እና

5/ የተጣለው አስተዳደራዊ ቅጣትና ቅጣቱ ተግባራዊ የሚሆንበትን ቀን የያዘ መግለጫ፡

## 18. ስለ ይግባኝ

1/ ተጠሪው በተወሰነበት በሁሉም ወይም በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ወዲያውኑ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የሚቀርበው የይግባኝ ማስታወቂያ በጽሑፍ ሆኖ በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ግኝት፣ ድምዳሜ እና/ወይም ተቃውሞ የቀረበበትን አስተዳደራዊ ቅጣት ማያዝ አለበት፡፡

2/ ይግባኙ የመጀመሪያው ውሳኔ ወይም ሌላ ሂደቱን የሚቋርጥ ትዕዛዝ ከተሰጠበትና ውሳኔው በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ለችሎቱ ፀሐፊ በሚቀርበው የይግባኝ ማስታወቂያ ይጀምራል፡፡ የመጀመሪያው ወሳኔ ወይም ሌላ ሂደቱን የሚቋርጠው ትዕዛዝ የደረሰው በፖስታ ወይም በተላላኪ ድርጅት አማካኝነት ከሆነ ይግባኝ ባዩ ወገን የይግባኝ ማስታወቂያ ጊዜው በ3 ቀናት ሊራዘምለት ይችላል፡፡

3/ የችሎቱ ፀሐፊ የይግባኝ ማስታወቂያ መቅረቡን ለሌሎች ተከራካሪ ወገኖች ያሳውቃል፡፡

4/ ይግባኙ በአግባቡ ተዘጋጅቶ አጭር የይግባኝ ማመልከቻ ሆኖ ይቀርባል፡፡ ይህ አጭር የይግባኝ ማመልከቻ የይግባኝ ማስታወቂያ በቀረበ በ30 ቀናት ወስጥ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

5/ ይህ የተዘጋጀው የይግባኝ አጭር ማመልከቻ የደረሰው ሌላው ወገን በደረሰው በ30 ቀናት ወስጥ የምላሽ መግለጫ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

6/ የምላሹ መግለጫ በደረሰው በ14 ቀናት ወስጥ የመጀመሪያውን አጭር መግለጫ ያቀረበው ወገን ለምላሽ መግለጫው የምላሽ መግለጫ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

7/ ባለሥልጣኑ በራሱ አነሳሽነት ትዕዛዝ ካልሰጠ በስተቀር ተጨማሪ መግለጫዎች ማቅረብ አይፈቀድም፡

8/ የይግባኙ አጭር መግለጫ በተቀመጠው የጊዜ ወሰን ካልቀረበ ተቃዋሚው ወገን ይግባኙ ወድቅ እንዲደረግ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

9/ የባለሥልጣኑ ቦርድ ይግባኙን ከሰማ በኋላ በራሱ አነሳሽነት አስተዳደራዊ ችሎቱ በተገቢው አጭር ጊዜ ወስጥ ውሳኔውን እንደገና እንዲያይ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 19. የባለሥልጣኑ ቦርድ ውሳኔ

1/ የባለሥልጣኑ ቦርድ ውሳኔውን በጽሑፍ ይሰጣል፡፡ የውሳኔውን ግልባጭ ለተጠሪው ይሰጠዋል፡፡ ወሳኔውም በእያንዳንዱ ክስ ወይም አስተዳደራዊ ቅጣት ላይ የተወሰዱ ድምዳሜዎች እና ግኝቶችን በተጨማሪም በአስተዳደራዊ ችሎቱ ተጠሪው ጥሷቸዋል የተባሉ ድንጋጌዎችን ወይም ደንቦችን እና የተወሰደውን አስተዳደራዊ ቅጣትና አስተዳደራዊ ቅጣቱ ተግባራዊ የሚሆንበትን ቀን ማያዝ ይኖርበታል፡፡

2/ የባለሥልጣኑ ቦርድ ውሳኔ የባለሥልጣኑ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

## 20. የግብይት ተሳታፊዎች አቤቱታ ስለሚሰማበት ሁኔታ

1/ በባለሥልጣኑ ወሳኔ ላይ አቤቱታ አቅርቦ የመሰማት መብት በባለሥልጣኑ አዋጅና መመሪያ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች የተሰጠው ሰው ወሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ወስጥ ለአስተዳደር ችሎቱ በማቅረብ ማሰማት ይችላል፡፡

2/ የአስተዳደር ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ከሰማ በኋላ የባለሥልጣኑን ወሳኔ ሊያፀና፣ ሊያሻሽል፣ ሊሽር ወይም ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ወደሚመለከተው የሥራ ክፍል ሊመራው ይችላል፡፡

3/ ከዚህ በላይ ባለው ንዑስ አንቀጽ መሠት ችሎቱ በሚሰጠው ወሳኔ የማይስማማ ተከራካሪ ወገን ለባለሥልጣኑ ቦርድ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

4/ ለባለሥልጣኑ አስተዳደር ችሎት የሚቀርብ የማሰማት አቤቱታ በጽሑፍ ሆኖ በዚህ ክፍል በተወሰነው የጉዳዮች አወሳሰን ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች መሠረት የሚመራ ይሆናል፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ
## ስለ ሕግ ጥሰቶችና ቅጣቶቻቸው

1. ባለሥልጣኑ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘን ሰው ዕውቅና ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

2. ባለስልጣኑ በሚከተሉት ሁኔታዎች ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት በእያንዳንዱ ክስ ከብር 5,000/አምስት ሺህ/ ያላነሰ እና ከብር100,000/አንድ መቶ ሺህ/ ያልበለጠ ሆኖም በድምሩ ከብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ/ ያልበለጠ ቅጣት ሊጥል ይችላል፡፡

1/ ሆን ብሎ የባለሥልጣኑን አዋጅ ወይም በአዋጁ ማሰረት የወጡትን መመሪያዎች በሚጥስ ማንኛውም ሰው ላይ፣

2/ በባለሥልጣኑ ዕውቅና የተሰጠው ወይም ዕውቅና ሊሰጠው የሚገባው ሰው በደንበኛው ስም እንዲያስቀምጠው፣ ለዋስትና እንዲያስይዘው ወይም ለደንበኛው የምርት ግብይት ሥራ ወይም ወል ማስተማመኛ እንዲሆን ወይም ከዚህ ግብይት ወይም ወል ለደንበኛው የተገኘውን ወይም ከምርት ግብይቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ከደንበኛው የተቀበለው ዋጋው ከብር 100/አንድ መቶ/ የሚበልጥ ማንኛውንም ገንዘብ ወይም ንብረት በማዘበረ፣ በሰረቀ ወይም ለራሱ አገልግሎት ባዋለ ሰው ላይ፣

በዚህ ንዑስ አንቀጽ "ዋጋ" የሚለው ቃል የፊት ለፊት፣ የገበያን ወይም የወጭ ዋጋን ሲጣለከት በጀምላ ወይም በነጠላ ሆኖ የሚበልጠው ዋጋ ማለት ነው፡፡

3/ እያወቀና ሆን ብሎ በባለሥልጣኑ አዋጅ፣ ወይም አዋጁን መሠረት አድርገው በሚወጡ መመሪያዎች ወይም በባለሥልጣኑ ሌላ ትዕዛዝ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን፣ ሪፖርቶችን ወይም ሰነዶችን ወይም የምርት ገበያ አባል ለመሆን ወይም ከአንድ አባል ጋር ለመተባበር ወይም ለመጣመር ከቀረበ ማመልከቻ ጋር በተያያዘ የቀረቡትን ሰነዶች ሀሰተኛ ባደረገ ወይም ሀሰተኛ እንዲሆኑ ባደረገ ወይም ወሳኝ ፍሬ ነገሮችን ባሳሳተ ወይም መካተት የሚገባውን ወሳኝ ፍሬ ነገር ሳያካትት በቀረ ወይም መግለጫዎች እንዳያሳስቱ መካተት ያለባቸውን ነገሮች ባስቀረ፣

4/ ወሳኝ ፍሬ ነገሮችን ወይም ዕውነታዎችን ሆን ብሎ ወደ ሀሰተኛነት የሚለውጥ፣ የሚደብቅ፣ ሀሰተኛ፣ የፈጠራ ወይም የተጨበረበሩ መግለጫዎችን የሚጥር፣ ወይም የሚሸፍፍን፣ ለምርት ገበያው ሀሰተኛ፣ የፈጠራ የተጨበረበሩ መግለጫዎችን የያዙ መሆናቸውን እያወቀ ሀሰተኛ ጽሑፍ ወይም ሰነድ ባዘጋጀ ወይም በተጠቀመ ሰው ላይ፣

3. የምርት ገበያው፣ ማንኛውም ዳይሬክተር፣ ሠራተኛ፣ ወኪል ወይም የምርት ገበያው ተቀጣሪ ሥራውን ለማከናወን የተቀመጡትን ደንቦች እና ሁኔታዎች ካላከበረ፣ ባላስፈፀመ ወይም የምርት ገበያው ወይም ማንኛውም ዳይሬክተሩ፣ ሠራተኛ፣ ወኪል ወይም ተቀጣሪው የባለሥልጣኑን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡትን መመሪያዎች ወይም የባለሥልጣኑን ትዕዛዞች እየጣሰ ከሆነ ወይም ጥሰው ከተገኙ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡
/ሀ/ የምርት ገበያውን በተመለከተ ከጥሰቱ ክብደት እና መጠን ጋር የተመጣጠነ ሆኖ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት በእያንዳንዱ ክስ ከብር 5,000/አምስት ሺህ/ ያላነሰና ከብር 150,000/አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ/ ያልበለጠ ሆኖም በድምሩ ከብር 750,000/ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ/ ያልበለጠ ቅጣት፣

/ለ/ ዳይሬክተሩን፣ ሠራተኛውን፣ ወኪሉን ወይም የምርት ገበያውን ተቀጣሪ የሚጣለከት ከሆነ ከጥሰቱ ክብደትና መጠን ጋር የተመጣጠነ ሆኖም በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ከብር 10,000/አሥር ሺህ/ የማይበልጥ ቅጣት፣

4. የከፍያ ሚፀሚ ተቋም፣ ዳይሬክተር፣ ሠራተኛ፣ ወኪል ወይም የከፍያ ሚፀሚ ተቋም ተቀጣሪ የዕውቅናውን ደንቦችና ሁኔታዎች ካላከበረ፣ ካላስፈፀመ ወይም ተግባራዊ እንዲሆኑ አለማድረጉ ከተረጋገጠ ወይም የከፍያ ሚፀሚ ተቋም ወይም ዳይሬክተር፣ ሠራተኛ፣ ወኪል ወይም ተቀጣሪው የባለሥልጣኑን አዋጅ ወይም አዋጁን ተከትለው የወጡትን መመሪያዎች ወይም የባለሥልጣኑን ትዕዛዞች እየጣሱ ከሆነ ወይም ጥሰው ከተገኙ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡

/ሀ/ የክፍያ ሚዜፀሚ ተቋማትን በተማለከተ ከጥሰቱ ክብደት እና ማጠን ጋር የተመጣጠነ ሆኖ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት በእያንዳንዱ ክስ ከብር 5,000/አምስት ሺህ/ ያላነሰና ከብር 150,000/አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ/ ያልበለጠ ሆኖም በድምሩ ከብር 750,000/ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ/ ያልበለጠ ቅጣት፣

/ለ/ ዳይሬክተሩን፣ ሠራተኛውን፣ ወኪሉን ወይም የክፍያ ሚዜፀሚ ተቋማ ተቀጣሪ የሚማለከት ከሆነ ከጥሰቱ ክብደትና ማጠን ጋር የተመጣጠነ ሆኖም በማኛውም ሁኔታ ቢሆን ከብር10,000/አሥር ሺህ/ የሚይበልጥ ቅጣት፡፡

5. ማንኛውም የግብይት ፈጻሚ ወይም የግብይት ፈጻሚ ወኪል ወይም ሠራተኛ የባለሥልጣኑን አዋጅ ወይም አዋጁን ተከትለው የወጡትን መሚሪያዎች ወይም የባለሥልጣኑን ትዕዛዞች እየጣሰ ከሆነ ወይም ጥሶ ከተገኘ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፣

/ሀ/ የግብይት ፈፃሚን በተማለከተ ከጥሰቱ ክብደት እና ማጠን ጋር የተመጣጠነ ሆኖ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት በእያንዳንዱ ክስ ከብር 5,000/አምስት ሺህ/ ያላነሰና ከብር 100,000/አንድ መቶ ሺህ/ ያልበለጠ ሆኖም በድምሩ ከብር 500,000/አምስት መቶ ሺህ/ ያልበለጠ ቅጣት፣

/ለ/ የግብይት ፈፃሚውን ወኪል ወይም ሠራተኛ በተማለከተ ከጥሰቱ ክብደትና ማጠን ጋር የተመጣጠነ ሆኖም በማኛውም ሁኔታ ቢሆን ከብር 10,000 /አሥር ሺህ/ የሚይበልጥ ቅጣት፡፡

6. የምርት ገበያው፣ የክፍያ ሚዜፀሚ ተቋሙ፣ የግብይት ፈፃሚው ወይም ሌላ ሰው በባለሥልጣኑ አዋጅ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ መሚሪያዎችን ወይም ትዕዛዞችን በመተላለፍ ተግባር ወይም አድራጎት ተሰማርቶ የሚገኝ ወይም በማሰማራት ላይ ወይም ለሰማራ ማሆኑን ባለሥልጣኑ ካማነ ይህን ድርጊት እንዲያቆም ወይም ከተግባሩ እንዲያታቀብ ወይም የባለሥልጣኑን አዋጅችና በዚህ መሠረት የወጡ መሚሪያዎችን እንዲያከብር ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

7. ከላይ በተጠቀሰት አንቀጾች 2፣ 3፣ 4፣ እና 5 የተማለከተውን የገንዘብ መቀጮ ለመወሰን ባለሥልጣኑ የቅጣቱን ተገቢነት ከጥፋቱ ክብደት ጋር ማነፃፀር ይኖርበታል፡፡

8. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 2፣ 3፣ 4 እና 5 መሠረት የገንዘብ መቀጮው ማከፈል ካለበት የሚዌሻ ቀን ወዲህ ባሉት 15 ቀናት ወስጥ በበቂ ሁኔታ በነዚህ መሚሪያዎች መሠረት ይግባኝ ማላሉን ወይም የተባለውን መቀጮ ሙሉ ክፍያ ማከፈል ያለበት ክፍያ በ15ቱ ቀን የጊዜ ወሰኔ ሜዌሻ ክፍያው ከነወለዱ ማከፈሉን ካላስረዳ፣ ይህ ሰው በባለሥልጣኑ ዕወቅና ያለው ከሆነ ይኸው ዕወቀናው ወዲያውኑ ይታገዳል፡፡

9. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 2፣ 3፣ 4 እና 5 የገንዘብ መቀጮው የተወሰነበት ሰው ይግባኝ አቅርቦ ባለሥልጣኑ ባይቀበለው ወይም ይግባኙ ወድቅ ቢደረግ፣ የይግባኙ ፍርድ ከተሰጠ ከ30ኛው ቀን በኋላ የሚጨለግበትን መቀጮ ሙሉ ክፍያ ማከፈሉን ለባለሥልጣኑ ካላስረዳና በባለሥልጣኑ ዕወቅና ያለው ከሆነ ዕወቅናው ወዲያውኑ ይታገዳል፡፡

10. የገንዘብ መቀጮ እንዲከፍል የተወሰነበት ሰው ለይግባኝ ማቅረቢያ የተፈቀደው ጊዜ ካለፈ በኋላ ወይም ይግባኙ ከፀና በኋላ መቀጮውን ባይከፍል ባለሥልጣኑ አግባብ ያለው የማንግሥት አካል የተባለውን መቀጮ ማስከፈል ይችል ዘንድ ሥልጣን ባለው የፍርድ አካል ጉዳዩን እንዲያቀርብ ይሚሉታል፡፡

## <u>ክፍል አሥራ ሁለት</u>
## <u>የባለሥልጣኑ የአስቸኳይ ጊዜ ስልጣኖች</u>

1. በባለሥልጣኑ አዋጅ አንቀጽ 32 መሠረት ባለሥልጣኑ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ መኖሩን ካማነ የምርት ግብይቱን ለማጠበቅና ለሚጋጋት አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡

2. የባለሥልጣኑ የአስቸኳይ ጊዜ ስልጣኖች የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፣
   1/ በወል ወስጥ ያልተፈፀሙ ግዴታዎችን ማሰረዝ ወይም ማስተላለፍ፣
   2/ ማንኛውም በወል ላይ የሚደረግ ግብይትን ማቋረጥ ወይም ማገድ፣ ሜቸውም የገበያው ተሳታፊዎች በማንኛውም በሚያደርጉት ወል አፈፃፀም ዋስትና እንዲሆን የተለየ ተቀማጭ ገንዘብ እንዲያስቀምጡ ግዴታዎችን ማቀመጥ፣

3/ ማኽቸውም የገበያው ተሳታፊዎች በማንኛውም በሚያደርጉት ወል አፈፃፀም ዋስትና እንዲሆን የተለየ ተቀማጭ ገንዘብ እንዳያስቀምጡ ግዴታዎችን ማስቀመጥ፣

4/ የምርት ገበያው ከ5 የሥራ ቀናት ላልበለጡ ጊዜያት እንዲዘጋ ማዘዝ፣

5/ የምርት ገብያው የሚሠራባቸው የግብይት ቀናትና ሰዓታት ለአንድ ሙሉ ቀን መዘጋትን ሳይጨምር እንዲሻሻሉ ማዘዝ፣ እና

6/ የምርት ገበያው የምርት ገበያ ደንቦችን እንዲያሻሽል ወይም ተፈፃሚነታቸውን እንዲያግድ ትዕዛዝ ማስጠት፡፡

3. ባለሥልጣኑ በዚህ ክፍል ንዑስ አንቀስ 2(4) መሠረት የሰጠውን የምርት ግብይቱን የመዘጋት ውሳኔ ሊያራዝመው ይችላል፡፡ እያንዳንዱ የሚራዘመው ጊዜ ከ5 ቀናት መበለጥ የለበትም፡፡

4. ባለሥልጣኑ በአንቀጽ 2 መሠረት ለሚሰጣቸው ትዕዛዞችና ወይም ለሚወስዱ እርምጃዎች እንዲሁም በዚህ ክፍል አንቀጽ 3 መሠረት ለሚሰጡ የመዘጋት የማራዘሚያ ውሣኔዎች ምክንያቶቹን መግለፅ ይኖርበታል፡፡

5. የባለሥልጣኑ ቦርድ አባላትን ምልዓተ ጉባኤ አሟልቶ ስብሰባ መጥራት ተግባራዊ ሊደረግ የሚቻል ከሆነ የባለሥልጣኑን ቦርድ ሊቀመንበር እንዲሁም እርሱ በሌለ ጊዜ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የተሟላው የባለሥልጣኑ ቦርድ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተወሰዱትን እርምጃዎች የመጨረሻ ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በባለሥልጣኑ ስም እና በዚህ አንቀጽ በተመለከቱ የሥነ ሥርዓት ደንቦች መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል፡፡

6. ሊቀመንበሩ ወይም ዋና ዳይሬክተሩ የአስቸኳይ ጊዜ ስልጣኑን በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ ማጠቀም አይችልም፡፡

1/ አዲስ አበባ በወቅቱ ከሚገኝ የባለሥልጣኑ ቦርድ አባል ጋር ከተመካከረ እና ሌሎች የባለሥልጣኑ ቦርድ አባላት ጋር በስልክ ለመካከር በቂ ጥረት ካደረገ በኋላ፣ እና

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ሳይፈፀም በሊቀመንበሩ ወይም በዋና ዳይሬክተሩ እምነት (ሊቀመንበሩ በሆነ ጊዜ ከዋናው ዳይሬክተር ጋር፣ ከዋና አማካሪው ወይም ምክትሉ ወይም ተባባሪው እና ሊቀመንበሩ ወይም ዋና ዳይሬክተሩ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያስበው ሰው ጋር በመካከር) ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በፍጥነት እርምጃ መወሰድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው፡

7. ሊቀመንበሩ ወይም ዋናው ዳይሬክተር የባለሥልጣኑን የአስቸኳይ ጊዜ ስልጣን ተግባራዊ ካደረገ በኋላ በአንድ የሥራ ቀን ወስጥ የወሰደውን እርምጃ ምልዓተ ጉባኤው ለተሟላ የባለሥልጣኑ ቦርድ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የባለሥልጣኑ ፀሐፊም የተወሰደውን እርምጃ በባለሥልጣኑ መዝገብ ወስጥ ማዝግቦ ማስቀመጥ አለበት፡፡

8. የባለሥልጣኑ ቦርድ ቀጥለው በተመለከቱት ሁኔታዎች ማናቸውንት በሊቀመንበሩ ወይም በዋና ዳይሬክተሩ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት የተወሰዱትን እርምጃዎች በመጨረሻ ውሣኔዎችን ለማጽናት፣ ለማሻሻል፣ ለመለወጥ ወይም ወድቅ ለማድረግ ይችላል፡፡

1/ የባለሥልጣኑ ቦርድ አባል የሆነ ማንኛውም ሰው ጥያቄ ሲያቀርብ፣ ወይም

2/ በሌላ በማንኛውም ሰው የቀረበ አቤቱታን የተቀበለው ከሆነ፡፡

9. በዚህ ክፍል "አስቸኳይ ሁኔታ" ማለት አንድ ሁኔታ ወይም የአንድ ክስተት መፈጠርን ሲመለከት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

1/ ፍፁም ያልተጠበቀ ሁኔታ፣ ጦርነት ወይም ሽብር፣ ከአቅም በላይ የሆነ አጋጣሚ የሲቪል ሁከት፣ እሳት፣ ጐርፍ ወይም ፍንዳታ፣ የግብይት ሥራውን የሚያስተጓጉል የተፈጥሮ አደጋ፣

2/ የምርት ግብይቱ ሥራ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር የኢኮኖሚ የገንዘብና የፖለቲካ ቀወስ ወይም ሌላ በኢትዮጵያ ወስጥ የተፈጠረ ተመሳሳይ ሁኔታ፣

3/ በምንም ዓይነት ምክንያት ይፈጠር ለምርት ግብይት ወሎች ሥራ ከፍያለ የገበያ ረብሻ በማስከቱ ምክንያት ገበያው የአቅርቦትና የፍላጐት ኃይሎችን ማንፀባረቅ ሲሳነው ፣ እና

4/ በባለሥልጣኑ አስተያየት የክፍያ ተቋማት፣ የምርት ገበያው የሰየማቸውን የክፍያ ባንኮች ወይም ሌሎች የክፍያ ተቋማት መደበኛ ጤናማ አሠራር የሚያስተጓጉሉ ሌሎች ተፈላጊ ያልሆኑ የገበያ ሁኔታዎች ወይም አሠራሮች ሲኖሩ ወይም የምርት ግብይቱን ሥርዓት የጠበቀ የወሎች ግብይት አሠራር ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ወይም ሂደቱ እንዲቋረጥ ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎች ወይም ሁነቶች፡፡

## ክፍል አሥራ ሦስት
## ማስታወቂያዎችን ስለማስተም

1. ባለሥልጣኑ ማስታወቂያዎች በመደበኛና ሕጋዊ ጋዜጣ ወይም በሌላ ማንገድ ባለሥልጣኑ በሚወስነው ማንገድ እንዲታተሙ ያደርጋል፡፡

2. በዚህ ክፍል ከላይ በአንቀጽ 1 የተገለፀው ጠቅላላነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ማስታወቂያዎች እንዲታተሙ ያደርጋል፣
   1/ በሕግ መሠረት የወጡ መመሪያዎች እና በባለሥልጣኑ የወጡ የፖሊሲ ማገለጫዎች ወይም በባለስልጣኑ የተቀረጹና የፀደቁ አተረጓጎሞች ከነ ማሻሻያዎቻቸው፣
   2/ በየደረጃቸው የተለዩ የግብይት ፈፃሚዎች ማዝገብ፣ እና
   3/ የክፍያዎችን ሰንጠረዥ፡፡

## ክፍል አሥራ አራት
## የክፍያዎች ሠንጠረዥ

1. የክፍያ ሚፀሚ ተቋሞች ዕወቅና.............................. ብር 500
2. ለምርት ግብይት ፈፃሚዎች ዕወቅና.............................. ብር 200
3. ለብሔራዊ የምርት ግብይት ፈፃሚዎች ማህበር ዕወቅና ...... ብር 100

## ክፍል አሥራ አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**1. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች**

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ የወስጥ ደንብ ወይም አሰራር በዚህ መመሪያ በተማከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረወም፡፡

**2. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ቦርድ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**መጋቢት 1 ቀን 2000 ዓ.ም.**
**አዲስ አበባ**
**የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ቦርድ**